# የቆሮንቶስ መልዕክት መግቢያ ጥናት

## የመግቢያ ጥናት ዓላማ

ስለ ቆሮንቶስ ከተማ፣ቤተ ክርስቲያን እና ስለ መልዕክቱ አጠቃላይ እውቀት በማግኘት ለመልዕክቱ ጥናት ለመዘጋጀት እንዲረዳ

## መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስ 66 መጽሐፍት ያሉት ሲሆን ከ66ቱ 27ቱ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ናቸው። ከ27ቱ ሐዋርያው ጳውሎስ በእርግጠኝነት 13 መልዕክቶችን ጽፏል። 14ኛውን የዕብራውያንን መልዕክት እርሱ ወይም ሰው እንደጻፈ ይነገራል። ከእነዚህም 6ቱ እስር ቤት ከመግባቱ በፊት (ሮሜ፣ ገላትያ፣ 1ኛ እና 2ኛ ቆሮ፣ 1ኛ እና 2ኛ ተሰሎንቄ) ፣4ቱ ከቁም እስር ቤት (ኤፌሶን፣ቆላስይስ፣ፊልጵስዩስ እና ፊልሞና)፣ ሁለቱ በመካከል ከእስር ቤት ተለቆ (1ኛ ጢሞ እና ቲቶ) እና የመጨረሻ ተመልሶ በከባድ እስር በታሰረ ጊዜ ነበር (2ኛ ጢሞ)። ከ14ቱ መልክቶች አንዱን የ1ኛ ቆሮንቶስን መልዕክት በ55 ዓ/ም ጽፎታል። ሐዋርያው ይህንን መልዕክት የጻፈውም በወቅቱ እስያ ውስጥ ከምትገኝ ከኤፌሶን ከተማ እንደሆነ ይታወቃል (ሐዋ. 19፡10 ሐዋ. 20፡31)።

ቆሮንቶስ በአሁኑ ጊዜ በግሪክ ውስጥ የምትገኝ ከተማ ስትሆን በውቅቱ በባህር ዳር ወደብ የነበረች የንግድ ከተማ እንደሆነች ይታወቃል። ከተማው በጥንት ጊዜ በአካይያ አውራጃ ይገኝ የነበረ የሮማ ግዛት ነው። ይህ ከተማ በሥነ ምግባር እና በመንፈሳዊነት እጅግ የተበላሸ ነበር። ከተማው በተለያዩ የጣኦት አማልክት የታወቀ ነበር። ወደ አሥራ ሁለት የሚሆኑ አማልክትም በቆሮንቶስ ከተማ እንደነበሩ ይነገራል። ብዙ የጣኦታት ቤተ መቅደስም ነበሩት። ከእነዚህም ታዋቂዋ የአፍሮዲጡስ ቤተ ጣኦት ሲሆን የፍቅር አምላክ የምትመለከበት ቤተ ጣኦት ነበረች። ከክፉ አምልኮ አንዱ ዝሙት ነበር።“ቆሮንቶሳዊ” ተብሎ መጠራት ልቅ ከሆነ የዐመጻኝነት ሕይወት ጋር ተመሳሳይነት አለው። ለፈውስ አምላክ ደግሞ የተሰራ የአስክሌፐደስ የጣኦት ቤት ነበር። ለአይሁዶችም ደግሞ ምኩራብ ነበራቸው። አይሁዶች በምኩራብ አምላካቸውን ያመልኩ ነበር እንዲሁም ትምህርትና ማህበራዊ ኑሮም ያደርጉ ነበር። ለዚህ ከተማ ወንጌል በሐዋርያው ጳውሎስ የተሰበከው በሁለተኛው የሚስዮናዊነት ጉዞ ነበር (ሐዋ 18:1-21)። ጌታ ለጳውሎስ በራዕይ ተገልጦለታል፣ ብዙዎች እንደሚያምኑና የበረታ ተቃውሞ በተልዕኮው ላይ እንደማይኖር ተናገረው (ሐዋ. 18፡9-10)። ሐዋርያው ጳውሎስ አቂላንና ጵርስቅላን በዚህ ከተማ አገኛቸው። አቂላ እና ጵርስቅላ ያመኑ አይሁዶች ሆነው በድንኳን ሥራ በቆሮንቶስ

ተሰማርተው ነበር።እነርሱም በቀላውዴስ ቄሳር ከሮሜ በ49ዓ.ም እንዲወጡ ተገደው የወጡ ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ በከተማዋ ለአስራ ስምንት ወራት በአገልግሎት ቆይቷል (ሐዋ. 18፡11)።

**የመልዕክቱ ዓላማ፡-**

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ችግሮች እንደነበሩበት መልዕክቱ ይነግረናል። ለምሳሌ በመሪዎች መከፋፈል (1ቆሮ ከምዕ 1-4)፣ የሥነ ምግባር ውድቀት (ምዕ 5-6)፣ የጋብቻ ጥያቄ (ምዕ 7)፣ እውነተኛ የክርስትና ነጻነት (ምዕ 8-10)፣ በማህበር መካከል የአገልግሎት ሥነ ሥርዓት እና የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀም (ምዕ 11-14)፣ ስለ ትንሳኤ የተሳሳተ ትምህርት (ምዕ 15)። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ቤ/ክንቷ ችግሩን የሰማው ከተለያዩ ምንጮች ነበር ለምሳሌ 1. የቀሎኤ ቤተሰቦች (1ቆሮ 1፡11) 2. ከቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ጥያቄዎችን የያዘ ከተላከ ደብዳቤ (1ቆሮ 7፡1፣25፤ 8፡1፤ 12፡1፤ 16፡1፣12) 3. በግላዊ ጉብኙት ጊዜ ከእስጢፋኖስ፣ ፎርቱኔተስ፣ እና አቂከስ፣በመስማት (1ቆሮ 16፡17) ናቸው። ለዚህም ከቀሎዔ ቤተሰቦች በተገኘ መረጃ ከምዕራፍ 1-4 ለመጻፍ መነሻ ሆኗል። ከቤተ ክርስቲያን ተወካዮች በተገኘ የቃል መልዕክት (ማለትም፣ እስጢፋኖስ፣ ፎርቱናተስ፣ እና አቂከስ) 1ቆሮ 5-6 ለመጻፍ መነሻ የሆነ ሲሆን ለጽሑፍ ጥያቄዎች ደግሞ መልስ እንዲሆን በጥቅሉ ከምዕ 7-16 ተጽፏል።

ቤተ ክርስቲያኗ ለየለያዩ መሪዎች በመወገን ተከፋፍላለች፡ ማለትም የጳውሎስ፣ የአጵሎስ፣ የጴጥሮስ፣ እንዲሁም ምናልባት የክርስቶስ ወገን ሆነዋል (1 ቆሮ. 1፡12)። ቤተ ክርስቲያኒቱ በአመራር ዓይነት ብቻ አልተከፋፈለችም፣ በተጨማሪ ደግሞ በበርካታ የሞራል ጉዳዮች እና በመንፈሳዊ ስጦታ አጠቃቀምም ችግሮችም ጭምር ወድቃ ነበር። ሐዋርያው ምክሮችንና ማስጠንቀቂያዎችን የሰጠው ቀጥታ ከጌታ እና ከእራሱ መንፈሳዊ ብስለት እንደሆነ መልዕክቱ ያሳየናል (1ቆሮ 7:12)።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. 1ኛ የቆሮንቶስ መልዕክት መቼ እና ከየት እንደተጻፈ ተነጋገሩ።
2. ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ወንጌል ታስሮ ወይም ከመታሰሩ በፊት የጻፋቸውን መልዕክቶች ጥቀሱ
3. ስለ ቆሮንቶስ ከተማ አጠቃላይ ነገር ተወያዩ።

4. ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን መል ዕክት ለመጻፍ የቤተ ክርስቲያንቷን ችግር እንዴት እንዳወቀ ለቡድኑ አስረዱ
5. በቆሮንቶስ ቤ/ክ የነበሩትን ችግሮች እና የስህተት ትምህርቶች ተወያዩ
6. **ጸሎት፡-** የሚቀጥሉትን ጥናቶች ጌታ እንዲያስተምረን፣ የክፉ እጅ እንዳይገዳደረንና እኛም ሰንፈን እንዳንገኝ በመጸለይ የዛሬውን ጥናት እንጨርሳለን።

**ማሳሰቢያ፡-**

- ወገኖች እባካችሁ ወደ ጥናቱ ከመምጣታችሁ በፊት የዕለቱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እና ጥናቱን እንዲታነቡ በታላቅ ትህትና እንጠይቃለን
- የቆሮንቶስ መጽሐፍ ብዙ ጉዳዮች ያሉበት መልዕክት ስለሆነ አንዳንድ ጥያቄዎች ከከበደን ወይም ካልገባን በሚቀጥለው ቀን አጥንተን እንድንመጣና እንድንነጋገር እንመክራለን።
- ሁሉንም መልስ መሪው ይችላል ብለን ማሰብ ተገቢ አይሆንም። መሪው ለሚነሱ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ላይኖረው ይችላል።
- በርግጥ መሪዎች ሁሉም በሚገባ ተዘጋጅተው እንዲመጡ ያስፈልጋል
- ሁላችንም ተማሪዎች መሆናችንን አንዘንጋ።
- ከሁሉ በላይ ፍቅራችን ይበልጣል።

የጌታ በረከት ከእናንተ ጋር ይሁን!

የኢት/ወ/ባ/ቤ/ክ ትምህርት ክፍል
**214-703-0100 (ext 221)**

## ጥናት አንድ
## 1 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 1:1-9

**ዓላማ፡-**

እግዚአብሔር የጠራን በመንፈስ ቅዱስ ከራሱ፤ ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ እና ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ወደሚሆን የከበረ ህብረት መሆኑን በመረዳት፣ ለተጠራንለት ለዚህ ህብረት በሚመጥን ህይወት መመላለስ እንደሚገባን ለማሳሰብ ነው።

**መግቢያ፡-**

የዛሬው ጥናታችን በ1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 1:1-10 ባለው ክፍል ላይ የተመሠረተ ነው። በዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ በሚኖሩ አማኞች መካከል ለተነሱ የመለያየት እና የመከፋፈል ችግር ትምህርት ይሰጣል፤ ሲጀምርም አማኝ የተጠራው ከእግዚአብሔር፤ ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ፤ ከመንፈስ ቅዱስ እና ፤ ከቅዱሳን ወገኖች ጋር ኅብረት እንዲኖረው መሆኑን ያስረዳል ። ሰው በዘፈቀደ የጀመረው ሳይሆን እግዚአብሔር አስቦ የመሰረተው ኅብረት እንደሆነ በማሳየት፤ የዚህንም ህብረት መንፈሳዊ ምስጢርም የጠለቀ እና የከበረ መሆኑን በትኩረት ያስገነዝባል።

### የመወያያ ጥያቄዎች (1 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 1:1-9)

1. በ1ቆሮ.1:1 ላይ ጸሐፊው ስለ ራሱ የሚናገራቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? ተነጋገሩ
2. በ1ቆሮ.1፡2-3 ስለ አጥቢያ ቤተክርስቲያን እና የቅዱሳን ህብረት የተገለጸው እውነታ ምንድን ነው? ቤ/ክ የማን ናት (ማቴ 16:18)?
3. በጥያቄ ሁለት ውይይት መሠረት የቅዱሳንን ህብረት ከሌሎች ህብረቶች የሚለይባቸው ዋና ዋና ነገሮች ምንድ ናቸው?
4. በቁ.4 ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበት ምክንያት ምንድን ነው? ለምን?
5. ከቁ. 5-6 የቆሮንቶስ አማኞች በጌታ ማመናቸው ያስገኘውን ፍሬ ተነጋገሩ?
6. ከቁ. 7-8 መሰረት የጌታን መገለጥ በመጠባበቅ ለሚኖሩ አማኞች የተሰጠው ተስፋ ምንድን ነው ? ይህስ ምን ፋይዳ ይኖረዋል ትላለህ? ኤፌ 4:11-13

7. በቁ. 9 የቆሮንቶስ አማኞች ወደ ምን ህበረት እንደተጠሩ እና የመጠራታቸውም ሆነ በዚህ ህብረት የመጽናታቸው ዋስትናው ምን እንደሆነ ተወያዩ? ዮሐ 10:28-29
8. ወደ ክርስቶስ ህብረት መጠራት የሚለውን ሀሳብ አብራሩ።
9. ከዛሬው ጥናት የተማራችሁትን አካፍሉ

**መደምደሚያ**

ዛሬ በተመለከትነው ጥናት መሰረት የተጠራነው ወደ አባት ወደ ልጁም ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እና ወደ የቅዱሳን ኅብረት ነው። እንዲሁም በዝሙዝሙር በወንድሞች ህበረት እግዚአብሔር በረከቱን እና ህይወትንም በዚያ እንዳዘዘ ተጽፎልን እናያለን፤ ስለዚህም የዚህ ህብረት ተካፋዮች እንድንሆን የጠራንን እግዚአብሔርን ከልባችን ልናመስግነው ይገባናል፤ በዚህም ህብረት ውስጥም እንደሚገባ የመመላለስ ኃላፊነት የእያንዳዳችን መሆኑን መዘንጋት የለብንም፤

## ጥናት ሁለት
## 1 ቆሮንቶስ 1:10-17

### ዓላማ

አንድነት እና ህብረታችንን ሊከፋፍሉ ወይንም ሊለያዩ ከሚነሱ ጊዚያው ችግሮችን በመናቅ በአንድነት ተያይዘን በጌታ ፊት ልንቆምበት የሚገባ እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው፤

### መግቢያ

በዛሬው ጥናታችን የምንመለከተው ክፍል 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 1:10-17 ይሆናል። በዚህም ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ በሚኖሩት አማኞች መካከል ስለ ተፈጠረው መለያየት እና መከፋፈል መንስዔ የሆኑትን ችግሮች ጠቅሶ በማውጣት ያብራራ ሲሆን፤ የችግራቸው መንስዔ ከሆኑት ጉዳዮች ይልቅ በአንድነት እንዲሆኑ ጌታ ኢየሱስ የከፈለላቸውን ዋጋ ከፍ አድሮጎ በማሳየት ከመለያየት ይልቅ መተባበርን እንዲመርጥ ያሳስባቸዋል፤

የመወያያ ጥያቄዎች

1. 1ቆሮ.1፡10 የቆሮንቶስ አማኞች እንዲያደርጉት የተመከሩት ምንድን ነው? ምክሩንስ እንዴት ነው ተግባራዊ ማድረግ የሚቻለው ትላላችሁ? ኤፌ 4:3
2. በቁ.10 እንዳያደርጉት የተለመኑት ጉዳይ ምንድን ነው? መለያየት ሊፈጠር የሚችለው እንዴት ነው? (ሮሜ 16:17 1 ቆሮ 12:24-25 ቲቶ 3:10-11) ለተጨማሪ ግንዛቤ ቢነበቡ ጥሩ ነው።
3. 1ቆሮ.1፡11 የቀሎዔ ቤተሰቦች ለሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ቆሮንቶስ አማኞች ያስታወቁት ጉዳይ ምንድን ነበር? ይህስ በህብረት ውስጥ አማኝ ሊወጣው ስለሚገባው ኃላፊነት ምን ያስተምረናል?
4. የጥያቄ 3 ውይይት ሀሳብ ካልተጨበጠ ወሬ ከአሉባልታ የሚለየው እንዴት ነው?

5. 1ቆሮ.1፡12 መሠረት የቆሮቶስ አማኞች ማንነታቸውን ሊያያይዙ የሞከሩት ከማን ጋር ነበር? የዚህ ዓይነቱ ችግር መንስኤው ከምን የተነሳ እንደሆነ አብራሩት? ለተጨማሪ ማብራሪያ 1ቆሮ.12:12-13 ጥሩ ይሆናል።
6. በቁ.13 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ላቀረባቸው ሦስት ጥያቄዎች መልሱ ምንድን ነው? ስለ ክርስቶስ ትክክለኛ ግንዛቤ መጨበጥ በመካከላቸው ለተነሳው የመለያየት ችግር እንዴት ነው መፍትሄ ሊሆን የሚችለው? ለተጨማሪ ግንዛቤ ኤፌ.2:16-22፣ ቆላ2:2
7. 1ቆሮ.14-17 ሐዋርያው ጳውሎስ የተጠራበትን ዋና የአገልግሎቱን ኃላፊነት እንዴት ነበር ያቀረበው? ይህንስ ሲል የውሃ ጥምቀት አያስፈልግም ማለቱ ነው? ገላ 6:15 አገናዝቡ
8. በእነዚህ ቁጥሮች ሐዋርያው እየተከላከለ ያለው ሀሳብ ምንድ ነው?
9. ከዛሬው ጥናት የቀረላችሁን ነገር አካፍሉ። በተረፈው መደምደሚያውን በማንበብ በጸሎት አብቁ።

### መደምደሚያ

ከተለያዩ ቤተ እምነቶች የመጣን በመሆኑ ምክንያት አንዳችን ከሌላችን የምንለይባቸው ጥቃቅን የሆኑ ጉዳዮች ሊኖሩ እንደሚችሉ መካድ አይገባም። ይሁን እንጂ አሁን ባለንበት በዚህ ህብረት ጌታን በልብ አንድነት የምናመልክ እና እጅ ለእጅ በመያያዝ የምናገለግለው ልንሆን ይገባናል። ስለዚህ እግዚአብሔር የሰጠንን ኅብረት የመጠበቅ ኃላፊነት የጋራችን እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምራል። በመሆኑም መለያየትም ሆነ መከፋፈል በመካከላችን እንዳይፈጠር ለዚህ ኅብረት እየተጠነቀቅን በማስተዋል መመላለስ እና መኖርም እንድንችል ሁላችንንም ጌታ ይርዳን።

## ጥናት ሶስት 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 1፡18-31

### ዓላማ

ከሰው ጥበብ እና ማስተዋል ይልቅ እጅግ የሚልቀውን በእግዚአብሔር የተደረገልንን ጽድቅ፣ ቅድስና፣ ቤዛነት፣ በመገንዘብ ትምህርታችን፣ እምነታችን፣ አግልግሎታችን እና ትምክህታችን በእግዚአብሔር ጥበብ ላይ ብቻ መሆን እንደሚገባው ለማስገንዘብ ነው።

### መግቢያ

መቼውንም ቢሆን የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ጠንቅቆ ያወቀው ሰው የለም፤ ከሰው እውቀት እና መረዳት በላይ ይሁን እንጂ በስብከት ሞኝነት አምኖ የመዳንን ጥበብ በወንጌል ስብከት ላመኑት እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገልጦላቸዋል። ይንን እግዚአብሔር ለክብራችን ሰውሮት የነበረውን ጥበብ ማወቅና መረዳት የምንችልበትን መንፈሳዊ አቅም ወይንም ማንነት ዳግመኛ ከመንፈስ ቅዱስ በመወለድ አግኝተናል። በአንጻሩም ለዚህ ዓለም ጠቢባን እና አስተዋዮች ይህ እውቀት ተጋርዶባቸዋል ወይንም ተሰውሮባቸዋል ። ስለዚህም እውነት እግዚአብሔር ከልባችን እየባረከን በዚህ እውቀትና መረዳት እንድናድግ ጌታ ይርዳን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. **1ቆሮ.1፡**18፣ቁ. 23 እና ቁ. 24 መሰረት የወንጌል ስብከት ጭብጡ ምንድን ነው? ይህስ በወንጌል ምስክርነታችን ዙሪያ ምን ያስገነዝበናል ትላላችሁ?
2. በቁጥር 18፣ 23 እና 25 መሰረት ለወንጌል መልዕክት ከፍ ያለ ጥንቃቄ ሊደረግ የሚያስፈልግበት ዋና ምክንያት ምንድ ነው? ይህስ መልዕክት ላልዳኑት ሰዎች እንዴት ባለ መንገድ ነው መቅረብ የሚገባው?

3. **1ቆሮ.1፡**19-22 እግዚአብሔር የጥበበኞችን ጥበብ እና የአስተዋዮችን ማስተዋል ከንቱ ያደረገበትን መንገድ ተነጋገሩበት?
4. በዚህ ክፍል መሰረት የእግዚአብሔር ጥበብ ምንድ ነው?
5. **1ቆሮ.1፡**26-28 መሰረት የቆሮቶስ አማኞች መጠራታቸውን በአጽንኦት እንዲያስቡት የተፈለገበት ዋና ምክንያት ምንድን ነው?
6. ጥያቄ 5 ላይ በተጠቁሰው ጥቅሶች መሰረት የተጠሩትም ይሁን የተጠራነው ከምን ዓይነት ሁኔታ ነው? ተወያዩ
7. **1ቆሮ.1፡**28-31 እግዚአብሔር በቆሮንቶስ አማኞች ህይውት ውስጥ የሰራውን መንፈሳዊ ነገር በዝርዝር ተነጋገሩ?
8. በቆሮንቶስ ቤ/ክ ውስጥ በህብረታቸው መካከል የተነሳውን የመከፋፈል ችግር ቀደም ባሉት ቁጥሮች ከጠቀሰ በኋላ በቁ.28-31 ያለውን ሃሳብ ማስከተሉ የሚያመልከተው ነገር ምንድን ነው?
9. በዚህስ ዘመን ባለን ቅዱሳን መካከል የዚህ ዓይነቱ ችግር አለ ብላችሁ ታስባላችሁ? መፍትሔውስ ምንድ ነው?
10. ካዛሬው የውይይት ጊዜ የተማራችሁትንና መጸለይ የሚገባን ነገር ካለ አካፍሉ ደግሞም እንጸልይ?

## *መደምደሚያ*

በእግዚአብሔር ጥበብ እና አሰራር በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ በመወለዳችን ምክንያት የእግዚአብሔር ጥልቅ ምስጢር ነገርን መረዳት የምንችልበትን ማንነት ሆኖልናል፡፡ ከዚህ ዓለም ጠቢባን እና አስተዋዮች የተሰወረው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በመንፈስ በኩል ለእኛ ስለ ተገለጠልን የእግዚአብሔር ጥበብ ስለሆነው ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ዘወትር ልንባርከው እና ልናመስግነው ይገባናል፡፡

## ጥናት አራት
## 1 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 2:1-5

**ዓላማ፡-**

ከእግዚአብሔር ቃል ስለተማርነው እውነት ለህይወታችን እና ለሚሰሙን ሰዎች የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባን ለማስገንዘብ

**መግቢያ፡-**

በዛሬው የጥናት ክፍለ ጊዜ የምንመለከተው 1ቆሮንቶስ 2:1- 5 ያለው ክፍል ይሆናል፤ በዚህም ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ትምህርት እና ስበከቱ የተመረኮዘው በላቀ የሰው ጥበብ ላይ ሳይሆን ይልቁንም በወንጌል ማዕከላዊ እውነት ላይ መሆን በአጽንኦት ያስረዳል፤ ስለዚህም ለሚሰሙት እና ለትምህርቱ የሚያድረገው ከፍተኛ ጥንቃቄ ያሳየናል።

### የምዕራፍ ሁለት 1-5 አጭር ማብራሪያ

1ቆሮ.2:1-2 ላይ እጅግ ከፍ ካለው ከሰው ጥበብ ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ነገር የሚጠብብ/የሚበልጥ መሆኑን በቀደመው ምዕራፍ ላይ ጀምሮት የነበረውን ሃሳብ በማንሳት ወደ ቆሮንቶስ ተጉዞ በነበረ ጊዜ የወንጌልን ስብከት በቃል እና በጥበብ ብልጫ እንዳላቀረበላቸው ይልቁንም ለሰዎች ሞኝነት የሆነው ቢሆንም ሰዎችን ለማዳን እግዚአብሔር የመረጠውን የክርስቶስን መስቀል በመካከላቸው በነበረበት ጊዜ በድፍረት ያቀረበላቸው እንደነበር ያስታውሳቸዋል።

1ቆሮ.2:3 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ከእግዚአብሔር የተቀበለውን የወንጌል ስብከት አገልግሎቱን ከሰው ጥበብ እና ማስተዋል ጋር በመደባለቅ እንዳያቀርበው ብርቱ ፍርሃትና ጥንቃቄን ያደርግ እንደነበር ያመለክታል። ይሁን እንጂ አንዳንድ በዘመኑ የነበሩ የግሪክ ጠቢባን ስብከቱን ለማበላሸት ያቀረቡት መከራከሪያ ሃሳብ እንደነበር በመጥቀስ ሐዋርያውን ያስፈራውን ለመግለጽ ይሞክራሉ።

1ቆሮ.2:4 እና 5 መሠረት የቆሮንቶስ አማኞች እምነታቸው በእግዚአብሔር አሰራር ወይንም ጥበብ ላይ የተመሰረት እንዲሆን ሐዋርያው የወንጌል ስብከቱን በሰው ጥበብ ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስና ኃይል ላይ የተመሰረተ እንደነበር ያብራራል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በ1ቆሮ 2:1 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ አማኞች በሄደበት ጊዜ አገልግሎቱን በምን ዓይነት መንገድ ነበረ የፈጸመው? "በቃል እና በጥበብ ብልጫ አይደለም" ሲል ምን ማለቱ ነው? (1 ቆሮ 1:17,20-22)
2. 1ቆሮ.2:2 መሰረት ሐዋርያው ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን መረዳት እንዴት እንደገለጸው ተወያዩ፤ ይህስ መረዳት በአገልግሎቱ ላይ ምን ፋይዳ ነበረው? ገላ 3፡1 ጋር በማስተያየት ተወያዩበት
3. በቁ.3 ሐዋርያው እንዴት ባለው ሁኔታ በቆሮንቶስ አማኞች መካከል እንደተመላለሰ ተነጋገሩ? ይህስ ከምን የተነሳ ይመስላችሁሃል?
4. 1ቆሮ.2፡4 እና 5ን መሰረት በማድረግ ሐዋርያው ለትምህርቱና ለሚሰሙት ያደርግ የነበረው ጥንቃቄ ከምን የተነሳ እንደሆነ 1ጢሞ 4:16 በመነጻጸር ተወያዩ?
5. በእነዚህ ቁጥሮች (4 እና 5) መሠረት መንፈስን እና ኃይልን መግለጥ ማለት ምንድን ነው? ከ1 ተሰ 1፡5 ጋር ማነጻጸር ተመልከቱት
6. በዚህ ክፍል "በሚያባብል የጥበብ ቃል አልነበረም" የሚለውን መልዕክት እንዴት ትረዳላችሁህ? በዚህስ ዘመን እንዲህ ዓይነቱ ችግር ያለ ይመስላችሁሃል?
7. ከሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወት አንድ አገልጋይ ስለሚሰሙት ሰዎችም ሆነ ስለ ትምህርቱ ማድረግ ስለሚኖርበት ጥንቃቄ ምን ተመራችሁ?
8. እስካሁን ባየነው ጥናት መሰረት ወንጌልን ላልዳኑት በምንናገርበት ጊዜ ልንወስደው የሚገባን ዋና ጥንቃቄ ምንድን ነው? ለምን እንደሆነ መልሳችሁ አብራሩት?
9. ከዛሬው የጥናት ክፍል ለየት ያለ የቀረላችሁን ነገር አካፍሉ

**መደምደሚያ**

የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ለህይወታችን መመሪያ ማድረጋችን የመጀመሪያ ቁልፍ ነገር ነው። ከዚሁም ጋር ተያይዞ ከእግዚአብሔር የተማርነውን እውነት ለሌሎች ማካፍል ደግሞ ሌላው ቀዳሚው ኃላፊነታችን ይሆናል። ስለዚህ ከእኛ

የቀደሙት ነቢያት እና ሐዋርያት እንዳደረጉት ሁሉ ለህይወታችን እና ለትምህርታችን የሚገባውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልገናል። የሚያዩንም ሆነ የሚሰሙንን ለማዳን ጌታ የሰጠንን ይህንን ትልቅ አደራ እንድንወጣ ለእያንዳዳችን ጸጋውን ያብዛልን።

## ጥናት አምስት (1ቆሮ 2:6-16)

### ዓላማ

በሰው ምርምር እና ፍልስፍና ሊታወቅ የማይችለውን ከፍ ያለውን የእግዚአብሔር ነገር እንድንረዳ የመንፈስ ቅዱስ ሚና ከፍ ያለ እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው

### መግቢያ

በዛሬ የጥናታችን ክፍል የምንመለከተው 1 ቆሮንቶስ 2፡ 6- 16 ያለውን ክፍል ይሆናል ሲሆን በዚህም ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ሰዎችን በፍልስፍናቸው እና በጥበባቸው ምጥቀት እግዚአብሔርን ሊያውቁት የማይችሉ መሆናቸውን በግልጽ ያመለክታል።ይህም ብቻ ሳይሆን በምርመራቸውና በፍልስፍናቸው ምክንያትም ከእግዚአብሔር እውቀት የሚርቁ እንደሆኑም ያመለክታል፤ ቢሆንም የእግዚአብሔርን ነገር ለማወቅ ለአማኞች ያለ አንድ ተስፋ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው አብርሆት እንደሆነ ያስረዳል።

### የክፍሉ አጭር ማብራሪያ ( 1ቆሮ 2:6-16)

1ቆሮ.2:6 እና 7 ላይ ደግሞ እግዚአብሔር ከጥበብ ጋር ጠበኛ ሆኖ ሞኝነትን ብቻ የሚፈልግ ሳይሆን በበሰሉት መካከል ግን የሚሻረውን የዚህችን ዓለም ሳይሆን ለክብራችን ተሰውሮ የነበረውን የማይሻረውን የእግዚአብሔር ጥበብ በሚስጢር ይናገር እንደነበር ይገልጻል።

በቁጥር ስምንት ላይ ይህም ለክብራችን ተሰውሮ የነበረው የእግዚአብሔር ጥበብ ክርስቶስ ኢየሱስ እንደነበር በማሳየት የዚህች ዓለም ጠቢባን ግን አንዳቸውም ይህንን ጥበብ እንዳላወቁት ይልቁንም እንደሞኝነት እንደቆጠሩት ያመለክታል።

፲ቆሮ.2:9 ላይ ዓይን ያላየውን ጆሮም ያልሰማውን በሰው ልብም ያልታሰበውን እግዚአብሔር ግን ለሚወዱት ያዘጋጀው ይህንን ጥበብ እንናገራልን ይላል።

ቁጥር አስር አስራ አንድ ላይ ይህንን ተሰውሮ የነበረውን የእግዚአብሔር ጥበብ ጽድቅና ቅድስናም ቤዛነትም የተደረገበትን ክርስቶስ ኢየሱስን እግዚአብሔር ለሚድኑት በመንፈሱ በኩል እንደገለጸው ያሳያል፤ ይህም በሰው ውስጥ ያለውን ነገር ከሰው መንፈስ በቀር ሊያውቅ የሚችል እንደ ሌለ ሁሉ እንዲሁ ያለ እግዚአብሔር መንፈስ ይህንን ጥበብ ሊረዳው የሚችል እንደሌለ አስምሮበታል።

፲ቆሮ.2:12-13 ሐዋርያው አማኞች ይህንን ጥበብ እዲረዱና እንዲያውቁ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው መንፈስ ቅዱስ እንጂ የዓለምን የጥበብ መንፈስ እንዳይደለ ስላይደለ፤ መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊ ነገር ጋር በማስተያየት መንፈስ የሚያስተረንን እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አንናገርም ይላል።

ቁጥር አስራ አራት እና አስራ አምስት ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ስለሆነ አይቀበለውም በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊታወቅም እንደማይችል በመግለጽ ለመንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ለመመርመር የተሰጠው መሆኑን ያስምርበታል።

በቁጥር አስራ ስድስት ላይ በጥያቄ መልክ የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? በማለት ለአማኞች በመንፈሱ በኩል እንዲያውቁት እግዚአብሔር የሰጣቸውን ያመለክታል።

## ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በ፲ቆሮ.2:6-7 መሰረት ስለ እግዚአብሔር ጥበብ እና ስለዚህ ዓለም ጥበብ ልዩነት በዝርዝር ተነጋገሩበት።
2. በ፲ቆሮ.2:8 መሰረት የዚህ ዓለም አስተዋዮች የእግዚአብሔርን ጥበብ ሊረዱ ያልቻሉት ከምን የተነሳ ነው? ይህስ ወደ ምን እዲያመሩ አደረጋቸው? ለምን?
3. ቁ.9 በማንበብ ዋናውን ነገር ተነጋገሩ።
4. በቆሮ.2፥10 መሰረት እግዚአብሔር ይህንን የላቀውንና የከበረውን የጥበቡን እውቀት እንዴት ነው እንድናውቅ ያደረገን? ኤፌሶን 3:4-6፣ቆላ 1:27 በማንበብ ሐዋርያው እየተናገረ ያለው ምስጢሩስ ምን እንደሆነ ተወያዩ።

5. በቆሮ.2፡11 መሰረት የእግዚአብሔር ጥበብ በሰው አዕምሮ ሊታወቅ የማይችል መሆኑን ከምን ጋር በማነጻጸር ነው ጳውሎስ ያቀረበው? ለምን?
6. 1ቆሮ.2:12 እና 13 በማንበብ በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ የተወለድ ሰው የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ሊገነዘብ የሚችልበት መንገድ እንዴት ነው የተገለጸው? በስፋት ተወያዩበት
7. በ1ቆሮ.2:14-15 መሰረት ፍጥረታዊው እና መንፈሳዊውን ሰው በማነጻጸር የሁለቱን ልዩነት ልዩነት ተነጋገሩ። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?
8. በቁጥር አስራ ስድስት መሰረት "እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን" የሚለውን መልዕክት እንዴት ትረዱታላችሁ?
9. ከዛሬው ጥናት የተማራችሁትን ነገር ለቡድናችሁ አካፍሉ?

**መደምደሚያ**

በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን ቃል የምንማርባቸው እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ መንገዶች አሉ። ለእነዚህም እግዚአብሔርን ማመስገን በጣም አስፈላጊ ነው፤ እነዚህ ሁሉ መንገዶች ግን አብሮን እንዲሆን፣ ወደ እውነት ሁሉ እንዲመራን፣ እዲያስተምረን የተሰጠንን የመንፈስ ቅዱስን ሚና የሚተካ ምንም ነገር ሊኖራቸው አይችልም አይገባምም። ጌታም ቤተክርስቲያንን ለቃሉ እና ለመንፈስ ቅዱስ አደራ የሰጠበት ዋና ምክንያትም ይሄ ነው። ስለዚህ በህይወታችን መንፈስ ቅዱስን ልንጠማው ምሪቱንም ዕለት ዕለት ልንፈልገው ያስፈልገናል።

## ጥናት ስድስት

## 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 3፡1-23

**ዓላማ፡-**

አገልጋዮች ከእግዚአብሔር ጋር አብረው ሰራተኞች መሆናቸውንና የተሰጣቸውን ጸጋ ሳናበላልጥ የሁሉን ባለቤት ጌታን ማክበር እንዳለብን ማሳየት።

**መግቢያ፡-**

በምዕራፍ አንድ ጥናታችን፤ የቆሮንቶስ ሰዎች ለክርስቶስ የተቀድሱ፤ የጌታን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን የተጠሩ መሆናቸውን ተመልክተናል። እንዲሁም ከቁጥር 11 አንስቶ እስከ ቁጥር 17፤ በመካከላቸው ስለ ነበረው ክርክር አይተናል። የክርክራቸው ዋና ትኩረት ባገለገሏቸው አገልጋዮች ሥም

ጎራ ለይተው “የእኔ ይበልጥ” “የእኔ ይበልጥ” መባባለቸው እንደነበረም አስተውለናል።

በአጭሩ ምዕራፍ ሶስት እና ምዕራፍ አራት፤ ጎራ ለይተው ይናቆሩ ለነበሩት ቆሮንቶሳውያን የቀረበ የተግሳፅ፣የምክርና የትዕዛዛት ምዕራፎች ናቸው።

ከመልዕክቱ ጭብጥ ሃሳብ እንደምንገነዘበው፤ ምዕራፎቹ ሁለት አይነት ተደራሲዎች ማለትም ቤተ ምዕመናንና አገልጋዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው። ምዕራፍ 3:1-9፣ 16-23 እንዲሁም ምዕራፍ 4:8-20 ያለው ሃሳብ በጥቅሉ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያተኰረ ሲሆን ምዕራፍ 3:10-15 እንዲሁም ምዕራፍ 4፡ 1-7 ያለው ደግሞ አገልጋዮችን የሚመለከት ነው።

የቆሮንቶስ ቤ/ክርስቲያን ምዕመናን ገና ሕጻናት አልፎም ሥጋዊያንና ሰባዊ ፍጡር መሆናቸው ለሐዋርያው ሸክም ሆኖ እንደነበር ከምዕራፎቹ መረዳት እንችላለን። በተጨማሪም ራሳቸውን እንደ እግዚዝብሔር እርሻ እንዲያዩ ከተከለውና ካጠጣው ላይ ዓይናቸውን አንስተው የሚያሳድጋቸውን ብቻ እንዲያስቡ ያስገነዝባቸዋል። በሌላ መልኩ እያነጹ የነበሩት የህንጻው ሰራተኞች አገልግሎታቸውን ከጌታ እንደተቀበሉ እንዲያውቁ እንደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስም ህንጻው ለምን ተግባር እንደሚውል ያስተውሉ ዘንድ ያሳስባል።

በመቀጠልም መንፈሳዊ ሰው፤ ከእግዚአብሔር መንፈስ የሆነውን በመንፈስ የሚረዳና የሚቀበል፤ የክርስቶስ ልብ ያለው እንደሆነ አስረድቶ በአንጻሩ ፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር ነገር ሞኝነት የሚሆንበት፣ መመርመር ባለመቻሉ ሊያውቅና ሊቀበል የማይችል እንደሆነ ይዘረዝራል። በመቀጠልም አማኞች የእግዚአብሔር ሕንጻ እንደሆኑ አብራርቶ ራሱን ደግሞ እንደ ብልህ ግንበኛ፤ መሰረት ጣይ እንደሆነ ሲገልጽ እናየዋለን።

## የመወያያ ጥያቄዎች (1ቆሮ. 3፡1-23)

1. በዚህ ክፍል (ምዕ.3:1-23) ውስጥ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ እንዴት እንደተገለጸ ተወያዩ? ከምዕራፍ 1 ቁጥር 2 ጋርስ እንዴት ይነጻጸራል?
2. የቤተ ክርስቲያንቷ ሁኔታ በመልዕክቱ ጸሐፊ ላይ ያስከተለው ተጽኖ ምን ነበር?
3. “ገና ሕፃናት… ሥጋውያን… ሰብአዊ ፍጡር ብቻ” ያሰኛቸው ዋና ጉዳይ ምን ነበር? ችግራቸው ምንድ ነው?
4. ጸሐፊው በቁጥር 5 ላይ ያነሳቻቸው ጥያቄዎች ዓላማ ምን ነበር? የቆሮንቶስ አማኞች እንዲያዩለት የፈለገው ጉዳይ ምንድ ነው?

5. በዚህ አንቀጽ ውስጥ፤ ቤተ ክርስቲያንቷን በተመለከተ፤ የሰዎች ድርሻና የእግዚአብሔር ድርሻ እንዴት እንደ ተገለጸ ተወያዩ? በድርሻዎቹ መካከል ያለው ብልጫና ልዩነት ምን ይመስላል?
6. በ1ቆሮ 3፡5-9 ባለው ሃሳብ ውስጥ፤ የቆሮንቶስ ሰዎች፤ ስለ ራሳቸው፣ ስለ አገልጋዮቻቸውና ስለ እግዚአብሔር እንዲያስትውሏቸው የተፈለጉ እውነታዎች ምን ምን ነበሩ? ተነጋገሩ
7. በቁጥር 10 እና በቁጥር 11 ላይ የሚብራራው ሀሳብ ምንድ ነው? " እንደ አንድ ብልኅ ግንበኛ " መሰረት መጣሉን የገለጸው ምንን ለማስገንዘብ ነበር? እንዴት ከወንጌል አገልግሎት ጋር ይገናኛል?
8. "መሠረትን ጣልሁ" የሚለው ሐረግ በቁጥር 6 ላይ "ተከልሁ" ከሚለው ጋር ተነጻጽሮ፤ በሐዋርያው ጳውሎስና በቤተ ክርስቲያንቷ መካከል ስለ ነበረው የግንኙነት ዓይነት ምን ያሰረዳና?

<u>ጊዜ ካልበቃን ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በሚቀጥለው ቀን ተወያዩ</u>

9. በመሰረቱ ላይ ለሚገነባ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ምን ነበረ? ለግንባታ የተዘረዘሩት መስሪያዎችና የሚፈትናቸው የፍርድ ዓይነት ምን ነበሩ?
10. በዚህ ክፍል ይቃጠላሉ ወይም አይቃጠሉም የምንላቸው ለይተን እንወያይ? ምን ትምህርት አለው?
11. በ1ቆሮ.3፡13-15 በተገለጸው ፍርድ ውስጥ፤ ጸኃፊው የመልዕክቱ ተቀባዮች እንዲያውቁት የፈለገው ሀሳብ ምንድን ነበር?
12. በ1ቆሮ.3፡16-17 የተሰጣቸው ስያሜ ምንድ ነው? ዓላማውስ ምንድ ነው?
13. በዚህ ዓለም ጥበብ ጥበበኛ የሆነ ሰው ራሱን እንደ ሞኝ ይቁጠር የተባለው ለምንድን ነበር? ራስን እንደ ሞኝ መቁጠርስ ማለት ምንማለት ነው?
14. በ1ቆሮ 3፡21-23 ያለው ሀሳብ ከሙሉ ክፍል ጋር ምን ግንኙነት አለው?
15. 1ቆሮ 3:1-23 ዋና መልዕክት ምንድ ነው?
16. 1ቆሮ 3 ዛሬ ለግል እና ለቤ/ክ ምን ትምህርት ያስተምራል?
17. ላዛሬይቱ ቤ/ክ ዛሬ የጸሎት ጊዜ ይኑረን።

***መደምደሚያ***

የቆሮንቶስ አማኞች በብዙ ችግር ውስጥ የነበሩ መሆናቸው የታወቀ ነው። ቢሆንም እግዚአብሄር መፍትሔ እየነገራቸው ይገኛል።በዘመናችን ያለችውን ቤተ ክርስቲያን (እኛን)

ሳናስብ ቆሮንቶስን ማጥናት አንችልም። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከእኛ ዘመን ጋር የሚገናኙ ብዙ ሃሳቦችን ማየት እንችላለን። በዚህ ጥናት መሰረት የራሴን ሕይወት እንዴት አየዋለሁ? የሚለውን ጥያቄ ለራሳችን በማንሳት፤ ለግላችን ሰለቀረልን ነገር ማሰላሰሉ እጅግ ጠቃሚ ነው። ከዚህ ጥናት የተነሳ በእኔ ሕይወት ሊቀር ወይንም ሊጨመር የሚገባው ነገር እንዳለ ማየቱ ጥሩ ይሆናል።

## ጥናት ሰባት
## 1 ቆሮንቶስ 4:1- 21

**ዓላማ፡-**

አገልጋዮች ከእግዚአብሔር ጋር አብረው ሰራተኞች መሆናቸውንና ያላቸውን ተገቢ ድርሻ ለይቶ ለማሳየት

**መግቢያ፡-**

በአገልጋዩች ስም (ጳውሎስ፣አጵሎስ፣ኬፋ) ተከፈፍለው የነበሩትን የቆሮንቶስ አማኞች ለማስታረቅ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ በአገልጋይና በአገልግሎት ዙሪያ ያሉትን በርካታ እውነታዎችን አውስቷል። አገልጋዮች ወደ እምነት የመጡባቸው ምክንያቶች፤ እንደ ተሰጣቸው ፀጋ መጠን ከእግዚአብሔር ጋር አብረው የሚሰሩ ሰራትኞች መሆናቸውን በምዕራፍ ሶስት ተመልክተናል። ምዕራፍ አራት የእነዚህ እውነታቸው ማሰሪያ እንዲሆን “እንግዲህ” በሚል ቃል (1ቆሮ 4:1 በአዲሱ መደበኛ ትርጉም) ይጀምራል “እንግዲህ ሰው ሁሉ እኛን እንደ ክርስቶስ አገልጋዮችና እንደ እግዚአብሔር ምስጢር ባለአደራዎች ሊቆጥረን ይገባል”።

በምዕራፍ አራትም እንደ እግዚአብሔር “ምስጥር” ባላ ዐደራዎችና እንደ ክርስቶስ ባሪያ እንዲቆጥሯቸው ያሳስባል። “ምስጢር” የሚለውን ሃሳብ የተለየ መረጃን ከማወቅ አንጻር የቀረበ ሃሳብ ሳይሆን፤ ለሁሉ ግልጻ ሆኖ በቀረበው እውነታ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን እቅድ ከማየት አንጻር የተሰጠ ነው ወይም እግዚአብሔር ሰው በራሱ ጥረት መኖር የማይችለው ጺጋ መግለጡ ማለት ነው። ለምሳሌ 1ቆሮ.1:18 ላይ “የመስቀሉ ቃል ለሚጥፉ ሞኝነት ነው፤ ለእኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሔር ኀይል ነው” እንደሚል፤ የመስቀሉ ቃል ለሁሉ ቢሰበክም፤ ሁሉም ግን በውስጡ ያለውን የእግዚአብሔርን የማዳን ኃይል እንዳልተቀበሉ

እንመለከታለን። ለምን? የመስቀሉ ቃል ዓለም "ጥበብ" ብላ ከያዘችው ሃሳቡ ጋር ስለማይሄድ፤ እንደ ነበር ከቃሉ እንረዳለን። ለዓለም ሞኝነት በሆነው የመስቀሉ ቃል፤ እግዚብሔር ማዳኑን መግለጡ፤ ያመኑት ብቻ የሚካፈሉትና የተካፈሉት ምስጢር ነው።

በ1ቆሮ.4:1 ላይ "ባለ ዐደራ" የሚለው ቃል "የቤት አስተዳዳሪ ወይም "መጋቢ" የሚለውን ሃሳብ ያሳያል። በ1ቆሮ 2:13 ላይ "ከመንፈስ በተማርነው ቃል እንናገራለን" ተብሉ የተጻፈው እውነት፤ ምስጢር የሚለውን ቃል ባለ ዓደራ ከሚለው ቃል ጋር ሊያቆራኝልን ይችላል። ባለ ዐደራ ታማኝ የሚሆነው፤ የተቀበለውን ሚስጢር፤ እንደ ተቀብለ ለተገባቸው ያከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው። እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች" የሚለው ሐረግ፤ የሚስጢሩ መጋቢዎች በቤቱ ላይ እንደ አለቃ የተሾሙ ፈላጭ ቆራጪች አለመሆናቸውን፤ አገልጋይ (ባሪያዎች) መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። ከቁጥር 3 እስከ ቁጥር 5 ያለውን፤ ስለ ፍርድ የሚያነሳውን ሃሳብ፤ በባለ ዐደራ ከሚጠበቀው ታማኝነት አንጻር ልናየው ይገባል። ባለ ዐደራ "ፍርድን" ወይም ታማኙቱ የሚመዘንበት ቀን እንዳለ ማሰብ እንዳለበት ምዕራፍ 3:13 እና ምዕራፍ 4:5 ላይ በመደጋገም ተጠቅሶል።

የቆሮንቶስ አማኞች ያበላለጧቸው የአገልጋዮች ዝርዝር በምዕራፍ 1 ከቁጥር 11 እስከ ምዕራፉ መጨረሻ ባለው ክፍል ውስጥ ተዘርዝረዋል። ከተዘረዘሩት መካከል፤ ራሱ ሐዋርያው ጳውሎስ እና አጵሎስን ጠቅሶ፤ እንዲህ ያለው መከፋፈል ሥጋዊነት እንደሆነ ፤ በምዕራፍ 3:5 ላይ ተመልክተናል። በምዕራፍ 4:6-7 ባለው ምንባብ መሰረት፤ ራሱንና አጵሎስን ብቻ እንደ ምሳሌ ማቅርቡ፤ ለቆሮንቶሳውያን ጥቅም እንደሆነ ይገልጻል። ይህም ጥቅም፤ "ከተጻፈው አትለፍ" (መጽሐፍ ከደነገገው) የሚለውን፤ ሌሎችን በቃሉ ወይም ቃሉ በሚፈቅደው መመሪያ ብቻ የማየት ትምህርት ነው።

በአገልጋዮች መካከል ያለው የአገልግሎት ልዩነት "የጸጋው መጠን" ውጤት፤ ደግሞም በጌታ የተወሰነ እንጂ ከሰው እንዳልሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ በተደጋጋሚ ገልጿል። "ጌታ ለእያንዳንዳቸው በሰጣቸው መጠን..." ምዕራፍ 3:5 "በተሰጠኝ ጸጋ መጠን" ምዕራፍ3:10 ይላል። ከአገልግሎት አድማስ አንጻር ሲታይ፤ ከጸጋው መጠን የተነሳ፤ አንዳንዶቸ "የበለጠ" ወይም ሰዎችን ተጽዕኖ የሚያደርግ አገልግሎት ሊኖራቸው ይችላል።ከዚህ የተነሳ "ገና ሕጻናት" የሆኑ ቅዱሳን እንደዚህ ያሉትን

አገልጋዮች ከሌላው አብልጠው ሊመለከቷቸው ይችሉ ይሆናል። አገልጋዮቹም በመመካት ፈተና ውስጥ ሊወድቁ ይችሉ ይሆናል። ሁሉ ከጌታ የተቀበሉት እንጂ በራስ ጥረት ያገኙት እንዳልሆነ ማሰብ፤ እንዲህ ላለው አደጋ መፍቴሔ እንድሆ ቃሉ ይናገራል።

## የመወያያ ጥያቄዎች (1ቆሮ 4:1-21)

1. በ**1ቆሮ 4:**1 ላይ ያለው ሀሳብ፤ የቆሮንቶስ ሰዎች አገልጋዮቻቸውን እንዴት እንዲያዩ ያዛቸዋል? ይህ ትእዛዝ በመካከላቸው ለነበረው መከፋፈል ምን መፍትሄ ይሰጣል?
2. “የክርስቶስ አገልጋዮች... የእግዚአብሔር ምስጢር ባለ አደራዎች” የሚሉት ሁለት ሃሳቦች፤ ለቆሮንቶስ ቅዱሳን የነበረው ትርጉም ምን ነበር? ተነጋገሩ
3. ከባለ አደራዎቹ ምን ይጠበቃል? ለምን?
4. 1ቆሮ 4፡3-5 ያለውን ሀሳብ፤ ከምዕራፍ 3-13-15 ካለው ፤ እዲሁም “ባለ አደራ” ከሚለው ጋር በማዛመድ፤ “ፍርድ” በሚለው ሀሳብ ዙሪያ የተሰጡትን ነጥባች በማንሳት እንወያይባቸው።
5. የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ተከፋፍለውባቸው የነበሩት የአገልጋዮች ስሞቻቸው በ1ቆሮ 1፡11 ባለው ክፍል ተዘርዝረዋል። የእነዚህ አገልጋዮች ኃላፊነታቸው ምንድ ነው?
6. በ1ቆሮ.4:6-7 ባለው ክፍል መሠረት አንድን ሰው ከሌላው አስበልጠው እንዳይመለከቱ እንዲሁም ማንም ራሱን ከሌላው አብልጦ እንዳይመለከት፤ የተከለከለበት ምክንያት ምንድ ነው? ለምን? እጅግ ጠቃሚ መልዕክት ነው።
7. ከቁጥር 8-14 ባለው ክፍል ውስጥ የተጠቀሱትን፤ የቆሮንቶስ ሰዎች የነበራቸውን ነገሮች እንዲሁም ሐዋርያቱ ስለ ወንጌል የከፈሉትን ዋጋ በመዘርዘርና በማነጻጸር ተወያዩባቸው። ለቁጥር 14 ትኩረት ከተሰጠ ከ8-14 ያለውን ሀሳብ መገንዘብ አይከብድም። የክፍሉስ ዓላማ ምንድ ነው?
8. በ1ቆሮ.4፡15 መሰረት ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ራሱን ያቀረበው እንዴት ነበር? በምዕራፍ 3 ቁጥር 6 ካለው መልዕክት ጋር እንዴት ሊዛመድ ይችላል?
9. የቁ.16 ምክር ለቆሮንቶስ አማኞች ምን ይጠቅማል/ምን እንዲያደርጉ ይመክራቸዋል?

10. ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ አይመጣም ብለው ያስቡ የነበሩት አንዳንድ ሰዎች ያደርጉት የነበረው ነገር ምን ነበር? ለእነርሱ እንዲሁም በአጠቃላይ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሐዋርያው መልዕክት ምን ነበር?
11. የዛሬው ጥናት ዋናው ዓላማ ምንድ ነው ምንስ ተረዳን?

## መደምደሚያ

በሰዎች መካከል መበላለጥን ማድረግ መከፋፍልን ይፈጥራል። ራስን ከሌላው አብልጦ ማየት፤ ከጌታ የተቀበሉትን ጸጋ መርሳት ትክክለኛ የወንጌል ትምህርት አይደለም። እንዲህ ያለው ኃጢያት እንዴት ነው በዘመናቸን እየሆነ ያለው? በዚህ ኃጢአት ሥር እንዳንወድቅ ከዚህ ጥናት ምን ቀርቶልን ይሆን? ራሳችንን እንዲሁም ሌሎችን እንደ ክርስቶስ ባሪያ እና እንደ እግዚአብሔር ሚስጢር ባለ አደራ አድርገን እንድናይ ከዚህ ጥናት የቀረልን ምንድን ነው? ለራሳችን እናሰላስላለን። ተባረኩ!

# ጥናት ስምንት
# 1ቆሮንቶስ 5:1-13
# ክፉውን ማስወገድ

**ዓላማ፡-**

የምዕመናን የህብረትን ህይወት በቅድስና ለመጠበቅ የሳተን በመገሰጽና በምክር የመመለስን አስፈላጊነትን ማስገንዘብ

**መግቢያ፡-**

በዚህ ምዕራፍ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያን በመሃከላቸው የነበረውን የሥነ-ምግባር ጉድለትን ያስተናገዱበት መንፈስና በተቃራኒው ሐዋርያው ጵውሎስ ስለ ችግሩ የነበረውን እይታ እንመለከታለን። ክፍሉ በአሕዛብ ዘንድ እንኳን ሊሰማ የማይገባ ነውር በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መሰማቱን ይናገራል። ስለዚህ በዚህ ጥናት የችግሩን ዓይነትና ቅዱሳን ሊኖራቸው ስለሚገባ አቋም የተሰጠውን አሳብ በማጥናት ለግላችን ሆነ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖቻችን ከጥፋት የሚጠብቀንን እውነት እንጨብጣለን።

በአሁን ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ እግዚአብሔር ቃል የማይሄዱትን ለማረምና እንደ አስፈላጊነቱ ለመቅጣት፥ ለመገሰጽ መሪዎች የሚቸገሩ መሆኑ ግልጥ የሆነ እውነት ነው። ምንም እንኳን በየአጥቢያችን ያለው ችግር የተለያየ ቢሆንም የቅዱሳን ጉባኤን ከነቀፋ ለመጠበቅ አማኞች በሥርዓት መሄድና ሌላውን ከነቀፋ መጠበቅ ይገባናል። የተገለጠን በደል ማውገዝ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ እርምጃን የመውሰድን አስፈላጊነትንም ከዚህ ምዕራፍ እንማራለን።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምናየው፥ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ስለነበረ የዝሙት ኃጢአት ነው። ምክንያቱ ግልጥ ባይሆንም ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱ ተገቢውን እርምጃ ከመውሰድ እንደተቆጠበችና ከማዘን ይልቅ እንደታበየች በመግለጥ በበደል የተገኘው ሊታረምና መንጋው ሊጠበቅ እንደሚገባ ይናገራል። ይህን ብቻ ሳይሆን ኅብረቱንም ይወቅሳል። የአባትን ሚስት ማግባት የኀላ ጥፋት ቢሆንም እንኳን የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ችግሩን ያስተናገደችበት መንፈስ ሐዋርያውን አስቆጥቶ ነበር። ስለሆነም ሐዋርያው ጳውሎስ ምንም እንኳን በሥፍራው በአካል ባይገኝም ከመንፈስ አንድነት የተነሳ በግለሰቡ ላይ ግልጽ የሆነ አቋም ነበረው።

ሌላው አብይ ነጥብ ኅብረቱን ከሚያጎድፍ የሴሰኝነት ሕይወት ራስን መጠበቅ አስፈላጊ እንደሆነ የሚያሳስበው ክፍል ነው። ይህ የኅብረቱን ጤና የሚያናጋ፣ የሌላውን ሕይወት የሚያጎድፍና በዓለም የሚኖራቸውን ምስክርነት ጉልበት የሚያሳጣ ነው።

## **የመወያያ ጥያቄዎች** (1ቆር.5:1-13)

1. በ**1ቆሮ.5:1** መሰረት- በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተሰማው ኃጢያት ምን ነበር? ከምንስ ጋር ነው የተነጻጸረው? ተወያዩ
2. በ1ቆሮ 5፡1-2 በህብረታቸው ስለተከሰተው የሥነ ምግባር ውድቀት የሐዋርያው አቋም ወይንም እይታ ምን ነበር?
3. በቁጥር 2 መሰረት ሐዋርያው የቆሮንቶስን ቅዱሳን የወቀሰበት ነጥቦች ምንድናቸው?
4. በ**1ቆሮ.5፡**3-4 ላይ የተገለጠው እርምጃ የት ሆኖ፣ በማን ስም እና በምን መንፈስ ነበር የወሰደው?

5. በ**1ቆሮ.5**፡5 መንፈሱና ሥጋውን አስመልክቶ ፍርዱ ምን ነበር? እንዴትስ ትረዳዋለህ/ ትረጂዋለሽ?
6. ከ**1ቆሮ.5**:6-8 ከእርምጃው አንጻር ስለ እርሾና በጉ ስለከፈለው ዋጋ ማንሳቱ ምን ያመለክታል?
7. በቁጥር 9-10 "አትተባበሩ" የሚላቸው ከምን ጋር ነው? ለምን? ማስተወሻ፡-1ቆሮ 5:9 ላይ ሐዋርያው የጠቀሰው ደብዳቤ 1ኛው ደብዳቤ እንደሆነ ይታወቃል።
8. በ**1ቆሮ.5**፡12 እና 13 ፍርድን አስመልክቶ ሰውን በሁለት ይከፍላል። ለምን? ሐዋርያው የሚያነሳው ሐሳብ በቁጥር ሁለት ላይ ላነሳው ወቀሳ እንዴት መፍትሄ ሊሆን ይችላል?
9. ከመካከላችሁ አውጡት የሚለውን የሐዋርያውን ትእዛዝ እንዴት ትረዱታላችሁ?
10. 2ቆሮ. 2:6-7፣ 7:9-12 ስናነብ ምን የሚያመለክተን ነገር አለ? ተነጋገሩ። ይህን እጅግ የድፍረት ኃጢአት ያደረግ የነበረ ሰው ተቅጥቷል ማለት ነው (2ቆሮ. 2:6-7)።
11. ከዛሬው ጥናት የተማርከውን ለቡድንህ አካፍል።

**መደምደምያ**

በቅድስና ለመኖር የተጠራን ስለሆንን ከቅድስና ህይወት ጎድለን እንዳንገኝ፤ በኅብረት በጌታ ጸጋ ልንበረታ እና ልንተጋ ይገባል። በበደል የሚገኙን ልንገስጽና ልንመክር የሚታረሙበትንም መንገድ መቀየስ ያስፈልጋል። ይህም ለጌታ ክብርን እንዲያመጣና ኅብረቱን ከነቀፋ በሚጠብቅ መንገድ ሊሆን ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ በበደል የተገኘውን በምህረት ማየትና በጽድቅ እንዲኖር የሚመለስና የሚጸናበትን መንገድ ልንፈልግ ይገባል።

# ጥናት ዘጠኝ
# 1ቆሮንቶስ 6:1-11
# ክፍል ፣ - መካሰስ በክርስቲያኖች መካከል

**ዓላማ፡-**

በአማኞች መካከል አለመግባባት ቢከሰት ጉዳዩን በቅዱሳን መካከል አቅርቦ መፍትሔ የማግኘትን ጥቅም ለማሳየት

**መግቢያ፡-**

ሐዋርያው በምዕራፍ አምስት በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን እርምን እንዲያስወግዱ መክሯል። በበደል የተገኘውን ግለሰብንም መገሰጽና መቅጣት እንደሚያስፈልግ ማኅበሩን በጥብቅ አሳስቧል። እርምጃን በመውሰድም አሳይቷል። አሁን ደግሞ በቤተሰብ ጉዳይና በቅዱሳን ኅብረት አለመግባባት ሲኖር የሚሸመግል እና የሚመክር አይጥፋ የሚልን ምክርን ይመክራል። ለዚህም ምክንያቶችን ይሰጣል።

በወዳጆችና በቤተሰብ መካከል የተከሰቱ ችግሮችን በተመለከተ የመፍትሄ ምክር የሚያመጣ ከታጣና ፈራጅ ፍለጋ ወደ ውጭ ከወጡ ሥር የሰደድ ድካምና የቅድስና ጉድለትን በኅብረቱ እንዳለ ያመለክታል። እነዚህ ወገኖች በራስ ወዳድነት ተውጠው ሌላውን የማስቀደም መንፈስ ጠፍቶ፣ ሌላውን በማታለል፥ ከአማኝ የማይጠበቅን ተግባርን ሲፈጽሙ ተገኝተው ነበር። ስለተገኘባቸው የቅድስና ጉድለትም አስመልክቶ ሆድን ለመሙላት መስመር መሳት፣ የሥጋ ስሜትን ለማርካት ቤተ መቅደሱን ማርከስ እንደሚታይባቸው ይመሰክራል።

በዚህ ምዕራፍ ሌላው ዋና ነጥብ እንደ አማኝ በጽድቅ በመኖር በዓለም ላይ ልንፈርድ ነው የተጠራነው እንጂ አለም ከእኛ የተሻለ ብያኔ ኖሯት የምታግዘን መስሎን በወንድሞች መካከል ጠብ ሲነሳ ፍትሕ ፍለጋ ወደ ዓለም መሄድ የለብንም በማለት ያስገነዝበናል። ለትዳር ችግራችንም ቃሉ መፍትሔ እንደሆነ አበክሮ ይናገራል። ስለዚህ ለቃሉ መገዛት አማራጭ የሌለው የሰላም መንገድ ነው።

## የመወያያ ጥያቄ (1ቆሮንቶስ 6:1-11)

1. በ1ቆሮ 6፥1 መሰረት ፍትህን ፍለጋ ወዴት ለሚል ጥያቄ ክፍሉ የሚሰጠን ሀሳብ ምንድን ነው? ከባልጀራው ጋር ሙግት ወይንም ችግር ያለበት ሰው ማድረግ ያለበት እና የሌለበት ምንድ ናቸው?
2. ከቁጥር 1-2 ባለው ክፍል ይደፍራልን? … አታውቁምን?… እና አትበቁምን? ሲል ምንን እያመለከተ ነው?
3. ቁጥር 3 አታውቁምን በማለት ሊያሳስባቸው የፈለገው ምንድን ነው? በዚህ ክፍል በመላእክት መፍረድ የሚለው ሀሳብ አማኞች በወደቁት መላእክት ላይ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ይህስ ምንን ያስተምራል?
4. ከቁጥር 4-6 በሚያቀርባቸው አራት ጥያቄዎች ሐዋርያው ሊያሳስባቸው ወይንም ሊያስጨብጣቸው የፈለገው ቁም ነገር ምንድን ነው? ከእነርሱ የምጠብቃቸው መልሱስ ምን ይመስላችሁሃል?
5. በ1ቆሮ.6፡6-8 የችግሩን መንሰኤን በተመለከተ ምንድን ነው ሊያሳያቸው የሚፈልገው? የቁ.8 ከባዱ ነገር ምንድ ነው?
6. በ1ቆሮ.6፡ 9-10 ስለተዘረዝሩ ኃጢአቶች ተነጋገሩ? በዛሬ ዘመንስ ይኖራል?
7. ከቁጥር 9-10 በማንበብ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የማይገቡ እነማን ናቸው? ለመግባትስ መንገዱ ምንድን ነው? በዝርዝር ተወያዩ።
8. በቁጥር 11 መሰረት ከላይ ከተገለጠው ፍርድ አምልጠን መንግስት ሰማያት ለመግባት የመግባታቸው ዋስትና ምንድን ነው?
9. ከዛሬው ጥናት ምን እንደተማርን አካፍሉ። ኃላፊነት መወጣት እንድንችል የጌታ ጸጋ እንዲበዛልን እንጸልያለን።

### መደምደሚያ

አልፎ አልፎ በአማኞች በመካከል ችግር ቢፈጠር እርስ በርስ በመወያየት በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ተመልክቶና ተነጋግሮ ዘለቄታዊ መፍትሔ መስጠት መንፋስዊነት ነው። ቅድስና እጅግ መሠረታዊ ነገር እንደሆነ ሁላችንም መገንዘብ አለብን።

## ጥናት አሥር
## 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6:12-20
## ክፍል 2 - የዝሙት አደገኛነት

**ዓላማ፡-**

ሰውነታችን የክርስቶስ አካል ብልትና የመንፈስ ቅዱስ መኖሪያ ስለሆነ በቅድስና መያዝ እንዳለበት ለማሳሰብ

**መግቢያ፡-**

ሐዋርያው ጳውሎስ በምዕራፍ አምስት በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን እርምን እንዲያስወግዱ መከሯል። በበደል የተገኘውን ግለስብንም መገሰጽና መቅጣት እንደሚያስፈልግ ማኅበሩን በጥብቅ አሳስቧል፤ እርምጃን በመውሰድም አሳይቷል። በዚህ ጥናት በመጀመሪያ ክፍል ደግሞ በቤተሰብ ጉዳይና በቅዱሳን ኅብረት አለመግባባት ሲኖር የሚሸመግል እና የሚመክር አይጥፋ የሚልን ምክርን ይመክራል። ለዚህም ምክንያቶችን ይሰጣል።

በዚህ ክፍል ደግሞ ለአማኝ የተሰጠ ነጻነትንና ቅድስናን በማነጻጸር በነገር ሁሉ ልንዘነጋው የማይገባን ሥጋችን የጌታ ስለሆነ ለሥጋ ምኞት አልፈን እንዳንሰጥ ያስገነዝበናል። እናም በአውዱ መሰረት ከትዳር ውጭ የሆነ የግብረ ስጋ ግኑኝነት በእግዚአብሔርን ህግ ላይ ማመጽ እንደሆነ ያሳያል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በ1ቆሮ.6፡12-13 ሐዋርያው ጳውሎስ በጌታ ስላገኘነው ነጻነት እና ስለ አማኝ ኃላፊነት የሰጠውን ምክር በሰፊው ተወያዩበት? “ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም” (1ቆሮ.6:12)።
2. በቁጥር 14 ሐዋርያው ለሥጋችን የትንሳኤ ተስፋ እንዳለ ከነማስረጃው መጥቀሱ በቅድስና ለመኖር የሚሰጠው ፋይዳ ምንድን ነው ትላላችሁ?

3. ከ፤ቆሮ.6፥15-20 ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስን ቅዱሳንን ከዝሙት እርኩሰት ሊጠብቃቸው ይችላል ብሎ የገለጻቸውን መንፈሳዊ እውቀት እና መረዳት በተመለከተ በስፋት ተነጋገሩበት።
4. ከቁጥር 13 "ሥጋ ለጌታ... ጌታም ለሥጋ" የሚለው አባባል ከቁጥር 17 እና 18 ካለው መልዕክት ጋር በማያይዝ ተወያዩበት።
5. የ፤ቆሮ.6፡15-20 ዋና ወይንም አውራ መልዕክት ምድነን ነው ትላለህ?
6. በቁጥር 19-20 አማኞችን "አታውቁምን?" በማለት በመጨረሻ የሚናገራቸው ነጥብ ምንድን ነው?
7. ከቁጥር 19-20 አንጻር የምዕራፉ አጠቃላይ አሳብ ምንድን ነው ትላለህ?
8. ከዛሬው ጥናት በተሻለ ሁኔታ ተረዳሁ የሚትሉት ነገር ካለ አካፍሉ።

## መደምደሚያ

ልንዘነጋው የማይገባን ነገር እርስበርስ መገፋፋትና ራስን በነጻነት ጥላ ልቅ ማድረግ አለማስተዋል መሆኑን ነው። ለፍትህ ወደ አለም መሮጥ ማደሪያውን በኛ ያደረገውን የተበረከውን የመንፈስ ቅዱስን ምክርና ተግሳጽ ቸል የማለት ፍሬ ነው። ሥጋችንን እንደ ፈቀደው ስንለቅ ትዳራችንን ያናጋል፣ ኅብረታችንን ያጎድፋል። በጽድቅ ለመኖር የተከፈለልን ዋጋ ያቃልላል። ጌታ ህይወቱን ሰጥቶ የታደገን በጽድቅ እርሱን እየመሰልን እንድንኖር ነው። ለአለም የጽድቅን ፋና (ብርሃን) እንድናበራና በራሳችን ክፉ ምኞት ተነድተን ብርሃናችንን እንዳናጠፋ እርስ በርሳችን ልንመካከር፥ ልንገሳጸጽ ይገባል።

# ጥናት አሥራ አንድ
## 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 7:1-16
## ክፍል 1 - በትዳር መቀባበልና አለመለያየት

**ዓላማ፡-**

አማኝ በማንኛውም የህይውቱ ገጽታ በዘመን ፍጻሜ ላይ እንዳለ በመገንዘብ ጌታን እያስከበረ መኖር ጥሪው መሆኑን ማሳሰብ።

**መግቢያ፡-**

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍም ከተቃራኒ ፆታ ጋር ሊኖር ስለሚገባ ጤናማ ኅብረት መንፈሳዊ ምክርን ይሰጣል። በአጠቃላይም ምዕራፉን አንዱ ከአንዱ ጋር በሚያያዙ አራት ክፍሎች ሥር እንመለከተዋለን። በቁጥር 1-6 በማግባትና ባለማግባት ጉዳይ አጠቃላይ ትምህርትን እናገኛለን። ከቁጥር 7-17 ባለው ክፍል ደግሞ ትዳርን ጤናማ በሆነ መንገድ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ምክሮችን ይሰጣል። በመቀጠልም ከቁጥር 18-24 ሁሉ በተጠራበት መጠራትና ጌታ ባስቀመጠው ሁኔታ ጌታን እያስከበረ እንዲኖር ይመክራል። በመጨረሻም በትዳር ላልተጠመዱትም ጌታን ደስ በሚያሰኝ ህይወት ለመኖር የሚረዳን ምክርን በቁጥር 25-40 ውስጥ አስቅምጧል። የዛሬው ጥናት በ1ቆሮ.7፡7:1-16 የተመሠረተ ይሆናል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በ1ቆሮ.7፡1-2 የሐዋርያው ምክር ምንድን ነው?
2. ከቁጥር 3-5 ባለትዳሮች አንዱ ለሌላው ሊያደርግለት ስለሚገባው የተገለጠው ምንድን ነው? ለምንስ?
3. ከቁጥር 6-7 “እንደ ፈቃድ እላለሁ” “እንደ ትእዛዝ አይደለም” የሚለውን ከምዕራፍ 6፡12 መልዕክት ጋር በማነጻጸር ተነጋገሩበት::
4. ሐዋርያው እንደኔ ሊሆኑ ሲልስ ምን ማለቱ ነው? ቁጥር 6-7
5. ከቁጥር 8-9 ላይ እነማንን የሚመክረው? ምክሩስ ምንድን ነው?
6. ላገቡ የተሰጠው ትዕዛዝ ምንድን ነው? ቁጥር 10-11

7. ከቁጥር 12-16 በትዳር ውስጥ አንዱ አማኝ ባይሆን፥ አማኝ የሆነው ስላለበት ኃላፊነት የተሰጠው መልዕክት ምንድን ነው? በዝርዝር ተነጋገሩበት።
8. ፩ቆሮ.6፡14-16 ላይ "ተቀድሷል" ፥ "ተቀድሳለች" ፥ "ታድፕ" እና "ታድን" የሚሉት ቃላት ምንድን ነው የሚያመለክቱት (የሚያስተምሩት)?
9. የዛሬውን ትምህርት ለቡድናችሁ አካፍሉ፤ጸሎትም እንጸልይ።

**መደምደሚያ**

ከዝሙት ጠንቅ ለመዳን አልሸነፍም ብሎ መፎከር ሳይሆን መሸሽ ነው መፍትሄው። ይህ እውነት ላላገቡ ብቻ ሳይሆን ላገቡም የሚሰራ ታላቅ እውቀት ነው። በሥጋ ፍላጎት ከመቃጠል ማግባት ተገቢና ማስተዋል ነው።

ካገቡ በኋላ ችግር አከተመ የሚባልበት ጉዳይ ስላልሆነ በትዳር ያሉ አንዱ ለሌላው ችግር ምክንያት ሳይሆን ሊመላለሱ ይገባል። መንፈሳዊ ልምምዳችንን ሰበብ አድርገን ከትዳር ጎዳኞቻችን ጋር ልንከላከልም አይገባም። በመስማማትና በመቀራረብ ከችግር ለመዳን ልንተሳሰብ ይገባል። የሥጋ ፍላጎታችንን ጌታን ወደሚያሳዝን ጎዳና እንዳይወስደን ልንነቃ ይገባል።

## ጥናት አሥራ ሁለት
## 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 7:17-40
## ክፍል 2 - ጌታ እንደወሰነልንና እንደ ጥሪያችን መኖር

**ዓላማ:-**

አማኝ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ጌታውን በሚያከብር ምሳሌያዊ ህይወት ሊመላለስ እንደሚገባ ማሳሰብ።

**መግቢያ:-**

በትዳር ይሁን ያለትዳር፣ ያገባም ይሁን ያላገባው ሁሉ እንደተጠራበት ጥሪ ሊመላለስና ጌታን ሊያስከብር እንደሚገባው አስገንዝቦ በሁለት ምሳሌዎች ነገሩን ያጠናክረዋል። ስለሆነም ግርዘትን እንደ ምሳሌ በመጠቀም የመገረዝና ያለመገረዝ ጉዳይ ጊዜያዊ ምልክት እንጂ የዘላለም ህይወት ጉዳይ እንዳልሆነ ያሳያል። የባርነትንም ሁኔታ በመጠቀም በወቅቱ ባሪያ የነበረ ሰው የጌታን ትዕዛዝ እየተከተለና በቃሉም እየተመራ ሳያመቻምች በታዛዥነት መኖር እንዳለበት ያስገነዝባል።

ለደናግልና ላላገቡም በእግዚአብሔር ቃል መሰረት እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያስገነዝባል። ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ ከሆነም ሳያገቡ ስለመቆየት ምክርን ይለግሳል። የዛሬው ጥናት በ1ቆሮ.7፥7:1-16 የተመሠረተ ይሆናል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በ1ቆሮ.7:17 እና 24 እያንዳንዱ እንደተጠራ ይመላለስ በማለት የሚሰጠው ምሳሌዎች ምንድን ናቸው?
2. በ1ቆሮ.7:12-22 መሠረት እውነተኛ ነጻነት ምንድ ነው?
3. በአምልኮተ እግዚአብሔር 12-24
4. በዚህ ክፍል መገረዝ ምንድ ነው? አለመገረዝስ? እንማን ናቸው?
5. በቁጥር 19 እና 30 የተሰጡ ሁለት ንጽጽሮች ምንድን ናቸው?
6. በቁጥር 19 እና 20 እንዴት መኖር እንዳለብን የተገለጹ ሁለት ነጥቦች ምንድን ናቸው?
7. በቁጥር 25 ሐዋርያው ለደናግልት ስለሚሰጠው ምክር መሠረቱ ምን እነደ ሆነ ነው የሚናገረው? ምንስ ያመለክታል?
8. ከቁጥር 25-31 ለአገቡና ላላገቡ ዘመኑን አስመልክቶ የሚሰጠው ምክርንና ዓበይት ምክንያቶችን
9. ከቁጥር 32-34 ያገቡና ያላገቡ በኑሯቸው ያላቸው አመለካከትና አላማ እንዴት ነው የተገለጠው?
10. በቁጥር 35 ምክሩን ለምን እንደሰጠ የሚያቀርባቸው ምክንያቶች ምን ምንን ናቸው?
11. ከቁጥር 36-40 ላላገቡ የሚያስተላልፈው ምክር ምንድ ነው?

**መደምደሚያ**

በዚህ ክፍል ጥናት ሰው ሁሉ ለራሱም ይሁን ለሌላው ጥቅም እና ለጌታ ክብር እንደተጠራበት መጠራት ይመላለስ የሚል መልዕክት ዋና ነገር ነው።፡ በዚህ ምዕራፍ ሐዋርያው ሰው ከቻለ በድንግልናው ጸንቶ መኖር መልካም ነው ይላል። አለማግባት በደል አይደለም፥ ሳያግቡ መቆየትም የመንፈሳዊነት መግለጫ ወይም ታላቅነት አይደለም። ዋናው ዘመን አጭር እንደሆነ አውቆ ጌታን በነገር ሁሉ ማስከበር፣ የጽድቅ አርበኛ መሆን ነው፥ የሁላችን ጥሪ።

## ጥናት አሥራ ሶስት
## የ1ኛ ቆሮንቶስ መዕራፍ 8:1-13
## እውቀታችን ሳያስታብየን፤ በፍቅራችን ደካማውን በማነጽ ጌታን ማክበር

**ዓላማ:-**

ምንም እንኳ በጌታ ባገኘነው ነጻነት ምክንያት በእግዚአብሔር ቃል ያልተከለከልነውን ሁሉ ለመለማመድ መብት እንዳለን ብናውቅም፣ ግን ሌሎች እንዳይሰናከሉ መብታችንን ስለሌሎች ፍቅር እና ስለ ጌታ ክብር መኖርን እንድንማር።

**መግቢያ:-**

የክርስትና ሕይወት የመተሳሰብ ሕይወት ነው! ይህንን ስንል ጳውሎስ በፊል 2:4 ላይ "እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፣ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ" ሲል እንዳሳሰበው ማለታችን ነው። ብዙ ጊዜ የኛን ጥቅም እስካሟላን እና ኃጢአት መስሎ እስካልታየን ድረስ የእኛ እርምጃ ሌላውን ወንድም አሰናከለው አላሰናከለው ብዙም አንጨነቅም። እንዲያውም "መብቴ ነው!" ሌላው ምን አገባው የሚል ምላሽ የተለመደ አባባላችን ሆኖ ይገኛል።

በተቃራኒው ደግሞ ጳውሎስ የለም፣ ከኔ መብትና ጥቅም ይልቅ የወንድሜ ጥቅም ይብለጥ የሚል አስተሳሰብ በሁላችን ዘንድ ሊነግስ ይገባል ሲል ያሳስባል።

ምንም ነጻነት ቢኖረን ነጻነታችንን ከኃላፊነት ጋር እንድንለማመድ እንጂ፣ የራሳችንን ነጻነት ብቻ በማሰብ እና የሌላውን ወንድም ትርፍ እና ጉዳት ከቁጥር ባለማስገባት እንድንመላለስ አለመጠራታችንን 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 8 ያሳየናል። በቆሮንቶስ ከተማ ብዙ የጣዖት አምልኮ የተለመደ ስለነበር ለጣዖት እንስሳ መሰዋት አንደኛው ሥርአት ሲሆን፣ ከመስዋዕቱ እና ከካህኑ የተረፈውን ሥጋ ለአምላኪው ግለሰብ ወይንም ቤተሰብ ይመለሳል። ይህን የተመለሰውን ሥጋ (በእነሱ አባባል የተቀደሰ ሥጋ) ፣ ጓደኛ እና ቤተዘመድ በተሰበሰበበት ወይም በቤተ አምልኮ ውስጥ  አልያም በግለሰቡ ቤት ውስጥ ይበላል (1ኛ ቆሮ 10:14-22 10፡27)።  ይህ ሥጋ ካስፈለገም በገበያ ቀርቦ ለሽያጭ መቅረብ ይችላል (1ኛ ቆሮ 10:25)።እንግዲህ በቆሮንቶስ የነበሩት አማኞች በዚህ ጉዳይ የተከፋፈለ እውቀት ነበራቸው። አንዳንዶች ይህንን ሥጋ ከማያምኑት ጋር በአምልኮተ ቤታቸው

ወይንም በማያምኑት ሰዎች ቤት አብሮ የመመገብ፣ ካስፈለገም ከገበያ ቦታ ገዝቶ የመጠቀም መብት እንዳላቸው ያምኑ ነበር። ሌሎች ደግሞ ለጣዖት የተሰዋ ሥጋ በምንም ዓይነት መንገድ መመገብ ኃጢአት እንደሆነ ያስቡ ነበር። ሐዋርያው ጳወሎስም ለዚህ ጥያቄ በዚህ ክፍል መልስ ሲሰጥ እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄ**

1. በ1ቆሮ 8፡1-13 ክፍል "እውቀት" የሚለውን ቃል ይደጋግማል። ይህ እውቀት ምን ዓይነት እውቀት ነው?
2. በ1ቆሮ 8፡1-13 መሠረት "ጠኦት" ምን እንደሆነ አብራሩ። ይህን ማወቅ ክፍሉን ለመረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው።
3. ከቁ 10-12 ባለው ክፍል ጳውሎስ "ደካማ" ሰው ወይንም "ሕሊና" እያለ ሦስት ጊዜ ሲጠቅስ ይገኛል። በዚህ ምዕራፍ መሰረት ደካማ የሚባለው ሰው ምን አይነት ነው? ሕሊናውስ ደካማ የተባለው ለምንድን ነው?
4. ደካማ ሰው ወይም ደካማ ሕሊና ሲል፣ ጠንካራ ሰው ወይንም ጠንካራ ሕሊና መኖሩን ያመለክተናል። ክፍሉ በቀጥታ ጠንካራ ሰው የሚለው ባይኖርም፣ ግን ጠንካራ ሰው የሚባለው በዚህ ምዕራፍ መሰረት ምን አይነት አማኝ ነው?
5. በሮሜ 14 1-3 እንዲሁም 14:5 ባለው መሰረት፣ ደካማ እና ጠንካራ በሚባሉት ክርስቲያኖች መካከል በ1ቆሮ 8 ከተጻፈው ሌላ ምን ልዩነት አለ? የሚያመሳስላቸውስ ምንድን ነው?
6. ለጣዖት የተሰዋ ምግብ በመብላት ወይንም በሮሜ 14 መሰረት ደግሞ ቀንን በማክበር እና ሥጋ በመብላት ያላቸው አመለካከት በጠንካራ እና በደካማ አማኞች መካከል ልዩነት እንዳለ ሁሉ የሚያመሳስላቸው ነገር አለ ብላችሁ ታስባላችሁ? (ለመልሱ ሮሜ 14:6-8 ያለውን አገናዝብ)
7. በ1ኛ ቆሮ 8 መሰረት **<u>በእውቀት ብቻ በመመላለስ እና በፍቅር በመመላለስ</u>** መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? የሚሻለውስ የቱ ነው? ለምን?

8. ጠንካራ የሆነው አማኝ ለጣዖት የተሰዋ ሥጋ መብላት በራሱ ኃጢአት እንዳልሆነ እያወቀ፣ ደካማ አማኞች ባሉበት ይህንን ሲያደርግ ኃጢአት የሚሆንበት ለምድን ነው?
9. ለጣዖት የተሰዋ ሥጋ በንጽህ ህልና ሳይጠራጥሩ በጸሎት ከተቀደሰ በራሱ ኃጢአት አይደለም፣ ነገር ግን ደካማው ክርስቲያን ሕሊናው እየወቀሰው ለጣዖት የተሰዋ ስጋ ቢመገብ ኃጢአት የሚሆንበት ለምድን ነው?
10. ዛሬ ባለንበት ዘመን በራሱ ኃጢአት ያልሆነ ግን ሌሎችን ሊያሰናክል የሚችል ምን ምን ምሳሌዎችን ማንሳት ትችላለህ?
11. ሌላው እንዳይሰናከል፣ መብቴን ትቼ የሌላውን ሕሊና እና ሕይወት ለመጠበቅ መኖር ያለብኝ ለምድን ነው?
12. መደምደሚያውን በማንበብ የዛሬውን ጥናት በጸሎት ማብቃት ይቻላል።

**መደምደሚያ**

እንግዲህ ክርስትና ከላይ እንዳየነው የመተሳሰብ ሕይወት ነው - “መብቴ ይጠበቅ!” ከማለት ይልቅ “ወንድሜ እንዳይጎዳ” በሚል የፍቅር ሂሳብ የምንኖርበት መለኮታዊ ድንጋጌ ነው። ከላይ እንደተመለከትነው፣ ከምግብ አንጻር እንኳ ሰዎችን እንዳናሰናክል እና ሕሊናቸውን እንዳናቆሽሽ እንዴት መጠንቀቅ እንዳለብን ያስገነዝበናል። ስለዚህም በክርስትና ጉዞአችን የሌላውን እያሰብን እና ስለሌላው እየተጠነቀቅን እንድንኖር ይገባናል።

## ጥናት አስራ አራት

## ፲ቆሮንቶስ ምዕራፍ 9፡1-27

የሐዋርያው ምሳሌያዊ ህይወት (ወንጌልን ለማድረስ ሁሉን መሆን)

**ዓላማ፡-**

ለወንጌል እንቅፋት እንዳንሆን ይልቁንም ለብዙዋች ያለእንቅፋት እንዲደርስ፣ ቢያስፈልግ መብታችንን ትተን፣ መሆን እና ማድረግ የምንችለውን ሁሉ አድርገን ሌሎችን መጥቀም እንደሚገባን ማሳሰብ።

**መግቢያ፡-**

ባለፈው ጥናታችን ምንም እንኳ ነጻነት እና መብት ያለን ሰዎች ብንሆንም ሌላውን ወንድም ላለማሰናከል ስለ ፍቅር መብትንም እንኳ መተው እንደሚገባ ተመልክተን ነበር። ከዚያው አሳብ ሳይርቅ በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ወንጌል በሚገባ እንዲሮጥ እና ወንጌል እንዳይከለከል መብትና ነጻነታችንንም እንኳ ቢሆን መተው ቢያስፈልግ መተው እንደሚገባ ከሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወት እንመለከታለን።

1ኛ ቆሮ 9:1-27 ባለው ክፍል ጳውሎስ እንደ ሐዋርያው እና የእግዚአብሔር አገልጋይ ያለውን ነጻነት እና መብቱን በገዛ ፈቃዱ እንዳልተጠቀመበትና ምንም ነጻ ሰው ቢሆንም ግን ራሱን ስለወንጌል ሲል ባሪያ እንዳደረገ እንዲሁም ከቁ 24-27 ባለው አስገንዝቦ ባገልግሎቱ እንደ ሯጭ እና እንደ ታጋይ (ቦክሰኛ) አበክሮ እየሰራ ሽልማቱን ለማሸነፍ እንደሚደክም ግን በትግሉ ዋጋ የለሽ ሆኖ እንዳይቀር ራሱን እየጎሰመ እንደሚያስገዛ ያስረዳል።

ከሚያገለግላቸው ደሞዝ ሊሰፈርለት እንደሚገባ እንደ ምሳሌ ወታደር በገዛ ገንዘቡ ጦርነት እንደማይሄድና የሚያገለግለው መንግስት ዋጋ እንደሚከፍለው፣ እግዚአብሔር በቃሉ ሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር ሲል ያዘዘው ስለ ከብቶች ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቤት የሚደክሙትን ማለቱ እንደሆነም እንረዳለን። በዚህ መሰረት እነ ሐዋርያው ጳውሎስም በመንፈሳዊ ነገር የሚያገለግሉ ከሆኑ፣ ተገልጋዮቹ ለሥጋቸው የሚያስፈልጋቸውን ሊሰፍሩላቸው እንደሚገባ ያሳያል።

በአጭሩ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ የሚነገረን ወንጌልን የሚያስነቅፍበት ነገር እንዳይኖር እና ለግል ጥቅም የሚሰብክ እንዳይመስልበት፦ አንደኛ ከሚያገለግላቸው ደሞዝ እንዲሰፈርለት መብት ቢኖረውም መብቱን ትቷል፣ ሁለተኛ ነጻ ሰው እንደመሆኑ እንደፈለገው መኖር ሲችል ሌሎች እንዳይሰናከሉ እና ብዙዎች ልባቸው ለወንጌል የተከፈት እንዲሆን ለሁሉ እንደ ባሪያ እንደሆነ ያሳየናል።

## መወያያ ጥያቄዎች (1ቆሮ.9፡1-27)

1. ሐዋርያው ጳውሎስ በምዕራፉ መጀመሪያ ሐዋርያው መሆኑን አንባቢዎቹ በሚገባ እንዲረዱለት ይፈልጋል? ለምን ይመስልሃል?
2. 1ቆሮ.9:3- 7 ባለው ጳውሎስ እየደጋገመ ስለ መብት ያወራል። በቁ. 12 እና 13 ደግሞ ከዚህ መብቱ ተጠቃሚ እንዳልሆነ ያስገነዝበናል። ይህንን እንዴት ማስታረቅ እንችላለን? ማስተማርስ የፈለገው ምንድነው?
3. ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን መብቱን ያልተጠቀመበት ለምንድን ነው?’
4. ባለፈው ሳምንት በምዕራፍ 8 ላይ ለጣዖት የተሰዋ ምግብ የመብላትን መብት ስለሌሎች እዲተዉ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች እንዳሳሰበ አይተናል። የዛሬው ጥናት ካለፈው ሳምንት ጋር የሚገናኝበት ነገር አለ? ምን?
5. ጳውሎስ መብቱን ብቻ ሳይሆን ነጻነቱንም እንደተወ ቁ. 19 ላይ ይናገራል። የምን ነጻነት ነው ጳውሎስ የተወው? ለምን?
6. ዛሬ ባለንበት ዘመን ሰዎች ስለ መብታቸው እና ስለነጻነታቸው ሲከራከሩ እና ሰዎች ሲሰናከሉባችው በሌሎች ነጻነት ምክንያት አማኝ ያልሆኑ ሰዎች ወንጌልን ከመስማት ሲሰናከሉ አይተህ ታውቃለህ?
7. ከዛሬው ጥናት ስለ አገልግሎት ምን ትማራለህ? በተለይ “አገልግሎት ትርፋችን ነው” በሚሉ አገልጋዮች እና “ለትርፍ እናገለግላለን” በሚሉ አገልጋዮች መካከል ምን ልዩነት ታስተውላለህ? ፡ይህስ ስለ አገልግሎት ምን ያስተምራል?
8. 1ቆሮ.9:22-23 እንደሚከተለው ይላል “22 ደካሞችን እጠቅም ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁ፤ በሁሉ መንገድ አንዳንዶችን አድን ዘንድ፥ ከሁሉ ጋር በሁሉ

ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ።23 በወንጌልም ማኅበረተኛ እሆን ዘንድ ስለ ወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ።” (9:22-23) በዚህ ቃል መሠረት በሚቀጥሉት ሳምንታት የወንጌል ሥራጭትን አቅዱ፣ አድርጉም። ስትሰበሰቡም ውጤቱን መስክሩ።

9. መደምደሚያ በማንበብ የዛሬውን ጥናት በጸሎት ማብቃት ይቻላል።

### መደምደሚያ

ዛሬ ባለንበት ዘመን መብትን እና ነጻነትን ስለ ወንድም ወይንም ስለ ወንጌል እና ስለ አገልግሎት መተው ለብዙዎች ከባድ ነው። ነገር ግን ከጳውሎስ ሕይወት እንደምንማረው፣ ኑሮ እና አገልግሎት ስለ ራሱ ሳይሆን ስለ ጌታ፣ ስለሌሎች ወገኖች እና ስለ ወንጌል ነው። እኛም ከዚህ ሕይወት በኑሮአችን ስለ ራሳችን መብት ብቻ ጥብቅና ከመቆም ይልቅ ስለ ሌላው ጥቅም፣ ስለጌታ አገልግሎት መብታችንን ብቻ ሳይሆን ነጻነታችንንም እንኳ ቢያስፈልግ ለመተው ፈቃደኛ እንድንሆን ይህ ክፍል ያሳስበናል።

## ጥናት አስራ አምስት
## 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 10፡1-13
## ክፍል አንድ - የእስራኤል ምኞትና ምሳሌነቱ

**ዓላማ፡-**

ክፉ ምኞት ውድቀትን ስለሚያስከትልና አልፎም እስከ ሞት የሚያደርስ ውጤት ስላለው ከዚህ የዓለማውያን አስተሳሰብና ድርጊት ተቆጥበን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ምሪት መኖር እንደሚገባን ለማስተማር

**መግቢያ፡-**

ይህ ክፍል ከ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 8 እና 10 መልዕክት ጋር የተያያዘ መሆኑን መርሳት የለብንም። በዚህ ክፍል በእጅጉን የሚዛመዱትን የክርስቲያን እውቀትና ነጻነትን ከክርስቲያን የፍቅር ኃላፊነት ጋር ሚዛን ለመጠበቅ አንድ አማኝ እንዲችል የተሰጠ ትምህርት ማብራሪያ ነው። በምዕራፍ 8 ለጣኦት ስለተሰዋ ነገር እውቀትና ነጻነት ቢኖርም ማለትም ምንም ዓይነት ጣኦት ከጌታ የሚበልጥ እንዳልሆነ እውቀት ቢኖረንም ስለሌሎች መዳን እና ስለልጎለበቱ አማኞች ነጻነታቸውን መተው እንዳለባቸው ይነግራቸዋል። እርስ በርስ በሚኖር ግንኙነት እርሱም አማኞችን በሚያጠናክርና ሌሎችንም ወደ ኢየሱስ በሚያመጣ ኑሮ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ ያዛቸዋል፡:

ለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ የእርሱን ነጻነት ስለሌሎች መዳን ትቶ እንዳገለገለ 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 9 ላይ እንደማብራሪያ እንደተጠቀመ የታወቀ ሲሆን በ1ቆሮ ምዕራፍ 10 ደግሞ የእስራኤላዊያንን ታሪክ እንደማብራሪያ ይጠቀማል ማለትም እስራኤላዊያን በታአምራት በውሃ ውስጥ እንዳለፉ እና በምድረበዳ መና እንደበሉ ነገር ግን ወደ ተለያዩ የጣኦት አምልኮ እንደዞሩ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት እና ትንሳኤ በታዓምራት የዳኑ አማኞችም እንዲሁ ወደ ጣኦት እንዳይዞሩ ያስጠነቅቃቸዋል። ነጻነት አለን ብለው ዞር እንዳይሉ ያስተምራቸዋል።

እስራኤላውያን በሙሴ እየተመሩ ወደ ተስፋይቱ ምድር በሚያመሩበት ጊዜ ሕጉ ማለትም የእግዚአብሔር ቃል በሚያዘው መሰረት እንደተጓዙና ሁሉም ከአንድ መንፈሳዊ ምግብ እንደበሉ እንዲሁም ከአንድም መንፈሳዊ መጠጥ እንደጠጡ ሆኖም እግዚአብሔር ከእነርሱ በሚበዙቱ ደስ እንዳልተሰኘ ከቁጥር 1-4 ያለው የምዕራፉ ክፍል ያብራራል። ይህም መብልና መጠጥ ክርስቶስ ነው።

በዙሪያቸውና በአካባቢያቸው ከነበሩት ዓለማውያን በመመልከት ቀንተው በጭፈራ የተደገፈ ግብዣ ያደርጉ እንደነበር፣ በዚህም ምክንያት አንዳንዶቹ ጣኦትን እንዳመለኩና አንዳንዶቹም ዝሙትን ይፈጽሙ እንደነበር በመዘዙም በብዙ ሺህ

የሚቆጠሩት እንዳለቁ ከቁጥር 6-10 ባለው ስንመለከት፤ ከቁጥር 11-13 ያለው ደግሞ እኛም ልዩ ልዩ ፈተና ቢያጋጥመን በመታገስ እንድንወጣው እንጂ ተጠላልፈን እንዳንወድቅ ምክር አዘል ማስጠንቀቂያን ይሰጠናል።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. 1ቆሮ.10፡1-2 ያለውን በተለይም በባሕር ውስጥ ስለመሻገራቸውን ከሙሴ ጋር ስለ መተባበራችው የታተተውን አብራሩ።
2. እግዚአብሔር እያዘጋጀላቸው አባቶቻችን በምድረ በዳ አንድ መንፈሳዊ ምግብ እንደበሉና አንድ መንፈሳዊ መጠጥም እንደጠጡ ይላል(1ቆሮ 10፡3-4)። ይህ መንፈሳዊ ምግብ  እና መንፈሳዊ መጠጥ ለቆሮንቶስ አማኞች ማን ነው? ምን ያደርግላቸዋል?
3. በቁጥር 5 መሰረት እግዚአብሔር በእስራኤል ያልተደሰተው ለምንድን ነው?
4. ያለፉት አባቶች ውድቀት ለቆሮንቶስ አማኞች ከዚያም ለእኛ ምን ትምህርት ይሆነናል (ቁጥር 6 እና 11)?
5. ዘጸዓት 32:1-6 በማንበብ ከዚህ ክፍል ጋር አገናኙ/አብራሩ። ከግብጽ ለወጡ ሰዎች ጠዖትን ማሰብና ማምለክ------------ነበር (ሩቅ/ቅርብ)። ለምን ምን ትምህርት አለው?
6. ከቁጥር 7-11 የተከናወኑትን የመተላለፍ ተግባራት ያብራሩ።
7. ክርስቲያን “ተደላድዬ ቆሜ አለሁ” ማለት ይኖርበታል (ቁጥር 12)? በዚህ ክፍል መሠረት የቆሮንቶስ አማኞች ልወድቁ የሚችሉት እንዴት ነው/ምን በማድረግ?
8. ፈተናን በተመለከት የእግዚአብሔርን ታማኝነት (ቁጥር 13) ያብራሩ። ቁ.14ን ምን ይገናኛል?
9. ዛሬ ምን ተማርን? አጠቃላይ ለእኛ ዛሬ ምን ትምህርት አለው? እናካፍል።

### መደምደሚያ

እንደ ክርስቲያን መመሪያችን የምናገኘው ከእግዚአብሔር ቃል እንጂ በአካባቢያችን ከሚታየው የዓለማውያን ድርጊት መሆን እንደለለበት በዚህ ክፍል የተመለከትነው የእስራኤላዊያን ታሪክ ጥሩ ማስገንዘቢያችን ነው። እስራኤላዊያን የጌታን ታአምራዊ መዳን በመርሳት ወደ ጣኦት ዘወር እንዳሉ እና መንፈሳዊ ልምምዳቸውንም እንደ ትምክህት ለማድረግ እንደሞከሩ እኛ ያለፈውን መንፈሳዊ ልምምድ እና ጥንካሬያችንን ረስተን ለወንድሞች ድነት እና ለእግዚአብሔር ክብር መኖር አለብን።

# ጥናት አስራ ስድስት
# 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 10:14-22
# ክፍል ሁለት - ከጣዖት ጋር አለመተባበር

**ዓላማ፡-**

ከክርስቶስ ጋር ሕብረት ያለው ክርስቲያን ጣዖትን አምላኪ ሊሆን እንደማይችልና እንደማይገባውም ለማመልከት

**መግቢያ፡-**

ከቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ታሪክ እንደምንገነዘበው የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ወደ እምነት የመጡት ከጣዖት አምላኪ ሕብረተሰብ ነው። የዕለት ተዕለት ተግባራቸውን በሚያከናውኑበትም ጊዜ እንደ አፖሎ፣ አስክሌጲስ፣ ዲሜጥሪ፣ አፍሮዲቴና በሌሎች ተባዕትና እንስት አማለዕክት ስም የቆሙ ጣዖታት ይጎበኙ ነበር። በተለይም አፍሮዲቴ በተባለች እንስት አምላክ ስም በቆመው ቤተ ጣዖት ውስጥ በርካታ ሴት አመንዝሮች ለዚሁ ተግባር ይገኙ ስለነበር ፈተናው ብርቱ ነበር።

በአንጻሩ የበረከትን ጽዋ ማለትም የጌታን እራት ሥርዓት የሚካፈል ከክርስቶስ ጋር ህብረት ያለው አማኝ በመሆኑ አምልኮተ ጣዖትንም ማስተናገድ እንደማይችል ክፍሉ በንጽጽሮሽ ምሳሌ ያብራራል።

## የመወያያ ጥያቄዎች (1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 10:14-22)

1. በመግቢያው መሰረት በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ስለነበረው አምልኮተ ጣዖታት ተወያዩ
2. ጣኦት ምንድ ነው? 1ቆሮ.10፡14 “ከጣዖት አምልኮ ሽሹ” የሚለውን አባባል አብራሩ
3. ከቁጥር 16-17 ባሉት ቁጥሮች መሰረት ስለ የጌታ እራት የተረዳችሁትን ተነጋገሩ
4. በሙሴ በኩል በተሰጠው የብሉይ ኪዳን ሕግ መሰረት መስዋዕቱን የሚበሉት ከመሰዊያው ጋር ሕብረት የነበራቸ እንዴት ነው (ዘዳ. 12:17-18) ከዚህስ እኛ ምን እንማራለን ?
5. የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ እንዲሁም የጌታን ማዕድና የአጋንንትን ማዕድ ማደባለቅ የማይቻለው ለምንድን ነው (ቁጥር 20-21)?
6. በቁጥር 22 መሰረት (ከዘጸ. 20:4-5 ጋር በማነጻጸር) ጌታን የምናስቀናው እንዴት ነው? ጌታ ይቀናል? አብራሩ

7. በዚህ ክፍል ስለ አማኝ የጣኡት እውቀትና የክርስትና ነጻነት እንደገና ተወያዩ። አማኝ መቼ ነው ነጻነቱን መተው ያለበት?
8. አንድ ሰው ከሌላ ኃይማኖት ሥጋ እንብላ ብሎ ቢጋብዝህ ምን ታደርጋለህ?

**መደምደሚያ**

በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሆነን የሰማያዊ የመንግስት ዜጎች ከሆንን በኋላ እግዚአብሔርንም ጣዖትንም ማምለክ አንችልም አይፈቀድምም። ብቻውን ያዳነንን አምላክ ብቻውን እያመለክን በተቀደሰ (በተለየ) ሕይወት መኖር ይጠበቅብናል እንጂ አንሸቃቅጥም። እንደዚሁም ለብዙዎች እንዳይድኑና እንዳያድጉ መሰናከያ መሆን የለብንም።

## ጥናት አስራ ሰባት
## 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 10:23-33
## ክፍል ሶስት - የአማኞች ነጻነት

**ዓላማ፡-**

የራስን ነጻነትና መብት ማየት ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ማሰብ አስፈላጊ እንደሆነ ለማስገንዘብ

**መግቢያ**

በዚህ ክፍል እንደ አማኝ ነጻ ብንሆንም የተፈቀደ ሁሉ እንደማይጠቅምና እንደማያንጽ ጠቅለል ባለ መልኩ እናያለን። የነገር ሁሉ ምንጭ ጌታ እንደሆነ በመረዳት በሥጋ ገበያ የሚሸጠውን ሁሉ መብላት እንደምንችልና ምናልባትም አማኝም ይሁን አለማዊ ለጣዖት የተሰዋ መሆኑን ቢነግረን ለህሊናው መጠንቀቅ እንደሚኖርብን እናስተውላለን። ማለትም አንድ ክርስቲያን ባለው እውቀት እና ነጻነት አንድ ነገር ከማድረጉ በፊት የሚያደርገው ነገር ለእግዚአብሄር ክብር እንደሚሆን/እንደማይሆን፣የእግዚአብሄርን ቤተክርስቲያን እንደሚያንጽ/እንደማያንጽ እና የማያምኑ ሰዎች ክርስቶስን አዳኝና ጌታ አድርገው እንዲቀበሉ የሚያደርግ ወይም የማያደርግ መሆኑን በጥንቃቄ ማየት አለበት። እንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች መጠየቅ አለባቸው።

## የመወያያ ጥያቄዎች (1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 10:23-33)

1. 1ቆሮ 10፡23-24 ባለው መሰረት የተፈቀደ ሁሉ የማይጠቅመውና የማያንጸው ለምንድን ነው?
2. በ1ቆሮ 10፡25 " በኅሊና ምርምር ሳትገቡ..." ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. ለጣዖት የተሰዋ መሆኑን እያወቀ ክርስቲያን የዚህ ዓይነቱን ሥጋ (ቁጥር 28) መብላት አለበት ወይስ የለበትም? ለምን?
4. በመብላታችንም ሆነ በመጠጣታችን ሌላም ስራ በመስራታችን መከበር ያለበት ማን ነው? ውጤቱስ ምን ይሆናል?
5. ለአይሁድም ሆነ ለግሪኮች መሰናክል ልንሆን የምንችለው እንዴት ነው? በዚህ ዘመንስ ?
6. 1ቆሮ 10፡33 መሰረት የሐዋርያው ጳውሎስ ጥረት ምን ነበር?
7. ሐዋርያው ጳውሎስ ለራሱ የሚጠቅመውን ሳይሆን ለሌሎች የሚጠቅመውን ያደርግ የነበረው ለምንድን ነው? "እኔ ደግሞ ብዙዎቹ ይድኑ ዘንድ ለጥቅማቸው እንጂ የራሴን ጥቅም ሳልፈልግ በሁሉ ነገር ሰውን ሁሉ ደስ እንደማሰኝ፥ ለአይሁድም ለግሪክም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ማሰናከያ አትሁኑ" (1ቆሮ 10፡32-33)።
8. ሌሎች እንዲያድጉ የሚረዳ እና ለጌታ ክብር የሚሆን ነገር ማድረግ እንድንችል ዛሬ እንጸልያለን።
9. በ1ቆሮ 10፡32-33 መሠረት ዛሬ እንድትጸልዩ እናበረታታለን።

### መደምደሚያ

በዕለት ተዕለት አካሄዳችን ሰዎች ሕሊናቸው እንዳይጎዳና ወንጌልን ከመቀበል ወደ ኋላ እንዳያፈገፍጉ ማሰብ ይጠበቅብናል።

"እኔ ደግሞ ብዙዎቹ ይድኑ ዘንድ ለጥቅማቸው እንጂ የራሴን ጥቅም ሳልፈልግ በሁሉ ነገር ሰውን ሁሉ ደስ እንደማሰኝ፥ ለአይሁድም ለግሪክም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ማሰናከያ አትሁኑ" (1ቆሮ 10፡32-33)።

# ጥናት አሥራ ስምንት
# 1ቆሮንቶስ ም ዕራፍ 11፡1
# ክፍል ፣ - ክርስቶስን እየመሰሉ መኖር

**ዓላማ፡-**

አማኞች በህይወታቸው የክርስቶስን ህይወት ምሳሌ በማድረግ በህይወታቸው ኢየሱስን እየመሰሉ እንዲሄዱ ለማሳሰብ።

**መግቢያ፡-**

በመሰረቱ 1ቆሮንቶስ 11፡1 ላይ ያለውን የመልክቱን ጭብጥ ስንመለከት የ1ቆሮ.10፡33 መልዕክት ቀጣይነት ሀሳብ እንዳለው የሚጠቁሙን ነገሮች እንዳሉ በግልጽ ያስረዱናል። በእርግጥ አንዳንዶች ለ11ኛው ምዕራፍ ቀጣይ ቁጥሮች ሀሳብም ይሆናል ብለው ይናገራሉ። በዚህ በመጀመርያው በ1ቆሮንቶስ 11፡1 የምዕራፉ መጀመሪያ ቁጥር ላይ ሐዋርያው ስለ ህይወት ተምሳሌነት ሁለት አቅጣጫዎችን መሰረት በማድረግ አስረግጦ ሲናገር እንመለከታለን። ሐዋርያው ይህንኑ ሀሳብ “እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ” በማለት ሲያበረታታ ይታያል። እነዚህ ሁለት አበይት የህይውት ተምሳሌቶችን ቅዱሳኑ በህይወታቸው እንዲለማመዱ አጽንኦት በመስጠት ይገልጻል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. 1ቆሮንቶስ 1፡1 ላይ ሐዋርያው ለቆሮንቶስ ቅዱሳን ሊያስጨብጣቸው የፈለገው ጉዳይ ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? 1ቆሮ 10:32-33 በማንበብ እና በማገናኘት ተወያዩ
2. በ1ቆሮ 10 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በምን ነበር ምሳሌ የሆነው? ዓላማውስ ምንድ ነው? ተነጋገሩ።
3. በዮሐወ 15፡13 ያለውን ህሳብ መሰረት በማድረግ ክርስቶስን መምሰል ያለብንን ባህርይ በመጥቀስ ለጥናት ቡድንህ አብራራ።

4. ፊል 2:5-8 ዮሐ 4፡34 ፣ 15፣10፣17፡4፣ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የተረዳህውን የክርስቶስን ባህርይ በመጥቀስ ተወያዩበት። ለእኛ ምን ትምህርት አለው?
5. በፊልጵስዩስ ሰዎች 3፡10-11 ላይ ሐዋርያው ክርስቶስን ለመምሰል ይመኝ የነበረው በምኑ ነው?
6. "እኔ ክርስቶስን እንደሚመስል እናንተም እኔን ምሰሉ" የምትልበት ድፍረትህ ምን ያህል ነው?
7. እራሳችንን በማየት ክርስቶስን እንዳንመስል ተግዳሮት የሆነብንን ነገሮች ምንድ ናቸው? አንተስ በክርስትና ህይወትህ ክርስቶስን የምትመስልባቸው ባህሪዎች አሉህ?
8. አንዳንድ ጊዜ ሌሎችን አማኞች "እኔን አትመልከት" እንላለን። ከዛሬው ጥናት ጋር ይህን አባባል እንዴት ማስታረቅ እንችላለን። ተወያዩ
9. መደምደሚያውን በማንበብ የዛሬውን ጥናት ማንበብ እንችላለን።

**መደምደምያ**

እንግዲህ ሐዋርያው "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ" ሲል እነዚህን ከላይ ለመጥቀስ የተሞከሩትን እና ብዙ ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ያልጠቀስናቸውን የክርስቶስን ባህርያት ምሳሌ አድርጎ በመውሰድ ጠንቅቆም በመረዳት እና በህይወቱም በመለማምድ "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ" ሊል ችሏል። ዛሬ እኛ ክርስቶስን የምንመስልበት ተምሳሌት ዋንኛው ክርስቶስ ቢሆንም የህይወት ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ በዙርያችን ደግሞ እንደደመና የከበቡን ኣያሌ ቅዱሳኖች እንዳሉ በመረዳት የህይወት እርምጃችንን በሚገባ ልንራመድ ይገባናል። ሐዋርያው "እኔን ምሰሉ" ሲል ከራሱ ማንነት ተነስቶ ሳይሆን እሱ ክርስቶስን የሚመስልባቸው ተምሳሌቶች በግልጽ በህይወቱ በመለመመድ ነው። ዛሬ እኛም የክርስቶስ ቤተሰቦች ይህንን የእርሱን ፈለግ በመከተል ሌሎችን ወደ ክርስቶስ የምንማርከበት ህይወት መኖር እንዳለብ ፍንትው አድርጎ ያሳየነል።

# ጥናት አሥራ ዘጠኝ

# 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 11፡2-16

## ክፍል 2 - ባህላዊ ወግን የተመረኮዘ መረዳት

**ዓላማ፡-**

በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ባለው የባህል እና አኗኗር ዘይቤ ፊጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ሳይለቅ ባህልን ከግንዛቤ በማስገባት እግዚአብሔር መመለክ እንዳለበት ለማስተማር

**መግቢያ**

ይህ ክፍል በታሪክ ብዙ የተማሩትን የቃሉን ተርጓሚዎችና የሥነ መለኮት አስተማሪዎችን እንዲሁም የአብያተ ክርስትያናት መጋቢዎችንም እያከራከረ እና እያነጋገር የቆየ ቢሆንም በዚህ ጥናት አዘጋጆች እምነት እና ትርጉም ክፍሉ በጠቅላላ ጥናት ምድብ በ1ኛ ቆሮ 12-14 ባለው ክፍል ማለትም በማህበር የአማኞች የአምልኮ ቦታ እና ጊዜ መኖር ስላለባቸው ሥርዓቶች ውስጥ ይጠቃለላል (ደግመው ያንብቡ)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ ሁለት አበይት ቁም ነገሮችን ለቅዱሳኑ ሲያብራራ እንመለከታለን። በመጀመሪያ በ1ቆሮንቶስ 11፡2 ላይ ቅዱሳኑ ለእርሱ ስለሚያስቡለትና በየጊዜው በክርስትና ጉዞቸው ስህተትን ቢፈጽሙም በአምልኮአቸው ባህልን ስለመጠበቅ ያስተማራቸውን ትምህርት ስለተቀበሉለት ምስጋናውን ለቅዱሳኑ ሲያቅርብ እንመለከታለን፣ “ወንድሞች ሆይ፥ በሁሉ ስለምታስቡኝና አሳልፌ እንደ ሰጠኋችሁ **ወግን** ፈጽማችሁ ስለ ያዛችሁ አመሰግናችኋለሁ” (1ቆሮ 11:2)።

በተጨማሪ ግን በሁለትኛ ሀሳቡ ደግሞ በ1ቆሮንቶስ 11፡3-16 አምልኮን፣ ስልጣንን እና መንፈሳዊ ህብረትን በማጣመር አስረግጦ እና አጠናክሮ ሲያብራራ እንመለከታለን። የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ የሴትም ራስ ወንድ እንደሆነ ከተናገረ በኋላ የክርስቶስም ራስ እግዚአባሔር እንደሆነ እንዲያውቁ በግልጥ ያሳስባል። የስላሴ መዋቅር የበታቸኝነትና የበላይነት ጉዳይ አይደለም።

ሐዋርያው ጳውሎስ በነበረበት ዘመን የነበረው ባህል በህዝብ ፊት እና በአምልኮ ስፍራ ራሷን የማትከናነብ ሴት እንደ አመንዛሪ ሴት ከመቆጠሯም በላይ የባሏንም ክብር እንደምታዋርድ ስለሚታሰብ ሚስቶች ከቤት በሚወጡበት ጊዜ እና

በአምልኮ ስፍራ ሁሉ ራሳቸውን ይከናነቡ እንደነበር ሁሉ ሐዋርያው ይህ አለባበስ በአምልኮም ስፍራ መተግበር እንዳለበት ለቅዱሳን ሲመክር እንመለከታለን። መላዕክትንም በሚመለከት ሙሉ ሥልጣናቸው በእግዚአብሔር የሆነና እግዚአብሔርን የማገልገል ሥልጣን ያላቸው የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደሆኑ ይገልጻል። እነዚህም መላዕክት በእውነተኛ የአምልኮ ሥፍራዎችም ይገኛሉ።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. 1ቆሮ.11፡2 ላይ "እንደሰጣኋችሁ **ወግን** ፈጽማችሁ ስለያዛችሁ አመሰግነችኋለሁ" በማለት የሚያመሰግንበት ወግ በማብራራት ለጥናት ቡድንህ አስረዳ "ወግ" የሚለውን ቃል በራስህ አገላልጥ ለጥናት ቡድንህ አስረዳ
2. ኢየሱስ በማቴዎስ 15፣1-20 ስለነቀፈው ወግ ተወያዩበት። ትክክል እና ትክክል ያልሆነውን ወግ ተነጋገሩ።
3. "ራስ" የሚለውን ሀሳብ እንዴት ትረዳዋለህ? ይህ ሀሳብ ከ"ስላሴ" ትምህርት ምሳሌ ጋር ምን ይገናኛል። በዮሐ 17፡4-6 መሰረት በማድረግ በመሀከለቸው ያለውን ህብረት አስረዱ
4. ኤፌ 5፡21-33 ያለውን ሀሳብ መሰረት በማድረግ በፍቅር እና በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተውን የወንድ በሴት ላይ ራስ የመሆን ስልጣን ለጥናት ቡድንህ ግለጥ። መዋቅር ብቻ እንጂ በኃጢአተኛ አዕምሮ የሚታሰብ የተጽ ዕኖ ሥልጣን አይደለም።
   - ከሁሉ በፊት ኤፌ 5:21 ትኩረት ይሰጥ በመቀጠልም
   - ስለ ሚስት "ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ" እና
   - ስለ ባል ደግሞ "ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት" ለሚለው ቃል ትኩረት ይሰጥ!
5. 1ቆሮ 11፡4-5 መሰረት በጸሎት ጊዜ በወንድ እና በሴት መደረግ ስለሚገባው ሥርዓት ምን በማለት መመሪያን ሲሰጥ እንመለከታለን? እነዚህ ሁለቱ ቁጥሮች ባህልን መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን መርሳት የለብንም። በእኛም በተለያዩ አከባቢ ያሉትን የአለባበስ ባህል ልዩነት ምስሌ መስጠት ትችላላችሁ።

## የሚቀጥሉትን የመወያያ ጥያቄዎች ወደሚቀጥለው ሳምንት ማሻገር ይቻላል

6. በጥያቄ ቁጥር 6 ላይ ያለውን ሀሳብ በአሁኑ ዘመን ካለችው የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርአት ጋር በማነጻጸር እንዴት ትመለከተዋለህ?
7. 1ቆሮ ፲፩፡7 "ሴት ግን የወንድ ክብር ናት" የሚለውን ሀሳብ እንዴት ትረዳዋለህ? ሴት በጉባኤ መካከል ባህልን ባልጣሰ በመከባበር መልኩ ካገለገለች ወንድ አይሸማቀቅም ማለቱ ከሆነ ዛሬ ይህ ቃል እየሰራ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ተነጋገሩ።
8. በወንድና በሴት መካከል ያለውን ተፈጥሮአዊ ትስስርን ዘፍ 2፣18-28 መሰረት በማድረግ በሰፊው ተወያዩበት
9. 1ቆሮ 11:10 የተጠቀሰው መላእክት ምንድ ነው? ዕብ 1:14 በማንበብ ስለ መላዕክት አፈጣጠር እና ተግባር በዝርዝር ተወያዩበት። በዚህ ክፍል የተጠቀሱ መላዕክት ቅዱሳን ሆነው እግዚአብሔር በሚመለክበት ቦታዎች እንደሚገኙ ለማሳሰብ ነው። ነገር ግን አንዳንዶች ወደ አምልኮ ቦታ የተላኩ ታዛብ የታወቁ ሰዎች እንደሆኑም ያምናሉ። ይህ ሁሉ ቢሆን ግን አምልኮ ቦታ ________ያስፈልገዋል (ሥርዓት/አለመገዛት?) ለምን?
10. የዛሬው ጥናት ዋናው ነገር ምንድ ነው? መደምደሚያውን በማንበብ መጨረስ ትችላላችሁ።

### *መደምደሚያ*

በዚህ ዘመን ይህን ሀሳብ በተመለከተ የተለያዩ አመለካከቶች ሊኖሩ ይችላሉ ሆኖም ግን በየትኛውም ዘመን ያሉ አማኞች በዘመናቸው ያለውን ባህልና ቋንቋ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር ሳይቃረን እንዲሁም ከእግዚአብሔር የተሰጠውን በሴት እና በወንድ መካከል ያለውን አንዱ ያለ አንዱ ሙሉ የማይሆንበትን፣ በፍቅር ላይ የተመሰረውተውን መለኮታዊ ህብረት መዕከል በማድረግ እግዚአብሔርን ማምለክ ይገባል። በሌላ አንጻር ደግሞ ጌታ በሚጠራበት በማንኛውም ስብሰባ ሥርዓት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ማወቅ መሠረታዊ ነገር ነው። እውነተኛ የአምልኮ ቦታ ጌታ ያለበት ቦታ ስለሆነ እጅግ የከበረ ቦታ ነው።

# ጥናት ሀያ

# 1ቆሮንቶስ 11፡17-34

## ክፍል 3 - በጉባኤ መካካል በጌታ እራት ላይ የታየ የተሳሳተ መረዳት እና እርማቱ

**ዓላማ፡-**

የጌታን እራት ሥርዓት ዓላማውን እና ምንነትን በማብራራት ለቅዱሳን በቂ ግንዛቤን ለማስጨበጥ

**መግቢያ፡-**

የቆሮንቶስ ቅዱሳን የአማኞች ማህበር (የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያንን) በወቅቱ የሚያምሷት ብዙ ችግሮች ነበሯት። ከእነዚህም ችግሮች መሀል አንዱ ስለ **<u>ጌታ እራት ሙሉ እውቀት ያለመኖር ችግር ነው።</u>** ይህም ችግር ተጠቅሶ የምናገኘው በ1ቆሮ 11፡ 17-22 ላይ ያለው በሀብታምና በድሃ እንዲህም በህብረተሰቡ ውስጥ የተከበረና ያልተከበረ በሚለው መሀል ያለው የጎላ ልዩነት ነው። ይህ ችግር ወደ ቤተ ክርስቲያን ከጌታ እራት ጋር ተያይዞ ዘልቆ በመግባቱ ሐዋርያው በ1ቆሮ 11፡2 ላይ ወጉን እንደያዙለት ሲያመሰግን በ11፡17-22 ላይ ደግሞ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ሲነቅፋቸው እና ሲገስጻቸው እንዲሁም ከገቡበት ስህተት ሲያስተካክላቸው እንጂ ሲያመሰግናቸው አንመለከትም።

የቆሮንቶስ አማኞች የጌታን እራት ይወስዱ የነበረው ስለነገሩ ምንም ሳይገባቸው እና አንዳንዶችም ሳይገባቸው(ያልዳኑም) በተጨማሪም ሥርዓቱን ሳይጠብቁ ለመደሰት እና ለመዝናናት እንደነበር ከሚያደርጉት ድርጊት መረዳት እንችላለን። ስለሆነም ይህ ድርጊታቸው ደግሞ እግዚአብሔርን ስለማያስደስተው ሐዋርያውን ተግሳጽና ምክርን ያዘለ ደብዳቤ እንዲጽፍ እንዳደረገው እንገነዘባለን።

የጌታ እራት ዓላማው የክርስቶስን ሞትና ትንሳኤ የምናውጅበትና ከቅዱሳን ጋር ያለንን ህብረት የምንካፈልበት ሥርዓት ነው። ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ሥርዓት አውጇል (ሉቃ 22:14-22)።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከሚያምሱ ችግሮች ሶስቱ ብቻ በማንሳት ተወያዩ። በዚህ ምዕራፍ 11 ሁለተኛ ክፍል ያለው ችግር ምንድ ነው?
2. በሉቃ 22:14-22 እና በማቴዎ 26፤26-28 መሰረት የጌታ እራትን አመሰራረትና መስራቹ ማን እንደሆነ ለጥናት ቡድንህ በዝርዝር አስረዳ? ዓላማውም ምን እንደሆነ ተወያዩ።
3. በ1ቆሮ 11፡18-19 መሰረት በማድረግ የጌታ እራትን በተመለከተ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበረው የችግሩ መጀመሪያ ምን ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ?
4. በ1ቆሮ 11፡20-24 እንደሚያመለክተው በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የጌታ እራት ዓላማን ሊያስታቸው ያስቻለው ዋነኛው ችግር ምንድነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
5. የጌታን እራት አስመልክቶ ችግሩን ለፈጠሩ ሰዎች ሐዋርያው የመከረበት አራት ነጥቦች ለጥናት ቡድንህ በዝርዝር አብራሩ?
6. በ1ቆሮ 11፡23 መሰረት የጌታ እራትን በተመለከተ ሐዋርያው ቀጥተኛ መገለጥ የተቀበለው ከማን ነው? ምንን ያሳያል?

<u>**የሚቀጥሉትን የመወያያ ጥያቄዎች ወደሚቀጥለው ሳምንት ማሻገር ይቻላል**</u>

7. የጌታ እራት ሚስጥራዊ ትርጉምን ሰፋ በማድራግ ለጥናት ቡድናችሁ ተናገሩ።
8. በ1ቆሮ 11፡26 መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን የጌታን እራት በወሰድን ጊዜ ሁሉ የሚያስታውሰን ምን ቁም ነገር እንድናደርግ ነው?
9. በ1ቆሮ 11፡27-29 አልገባቸውም ወይም አልተገባቸውም ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተወያዩ?
10. መረዳቱ ሳይኖረን የጌታ እራትን መውሰድ የምን ባለ እዳዎች እንድንሆን ያደርገናል ብላችሁ ታስባላችሁ ስለዚህ ባለእዳ ላለመሆን መፍትሄው ምን ይመስልሀል?
11. የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች የጌታን ሥጋና ደም ሳይለዩ ይህን ሥርዓት በመፈጸማቸው በእነርሱ ላይ ያመጣውን ችግር በዝርዝር ለጥናት ቡድንህ አስረዳ? ይህ ዓይነቱ ችግር እንዳይፈጠር መፍትሄው ምን ይመስላችሁሃል?

12. በ1ቆሮ 11፡33 መሰረት ሐዋርያው ስለ ጌታ እራት በተመለከተ ምን ምክር እንደሰጠ ተነጋገሩ?
13. የጌታ እራትን በተመለከተ በአጠቃላይ የተረዳኸውን መረዳት በዝርዝር ለጥናት ቡድንህ አስረዳ
14. የጌታ እራት ሥርዓት የሚጠራበትን የተለያዩ ስሞችን ጥቀስ?
15. የጌታ እራት ማለት ላንተ ምን ትርጉም አለው? እንዴትስ ትረዱታላችሁ?

## ***መደምደምያ***

የጌታ እራት ልክ ጌታ ታልፎ ሊሰጥ ባለበት ሌሊት በኢየሱስ በራሱ የተቋቋመ ስርአት መሆኑን መጽሀፍ ቅዱስ ይነግረናል። የዚህም ሥራዓት ዋናው ዓላማ ደግሞ የጌታ ስጋ ስለ ኃጢዓታችን መቆረሱን እና ደሙ ስለ ብዙዎች ለሀጥያት ይቅርታ የፈሰሰ የአዲስ ኪዳን ደም መሆኑን ሁል ጊዜ ከማስገንዘቡ ባሻገር ጌታ እስኪመለስ ድረስ ሞቱን ለአለም የምንናገርበት የማስታወሻ ደወል ነው። እንግዲህ ይህን ከጌታ የተቀበልነውን ሥራዓት በምንፈጽምበት ጊዜ ሁሉ የጌታ እራት አላማውን እንደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በመሳት በእግዚአብሄር ፍርድ ሥር እንደወደቁ እንዳንወድቅ ራሳችንን በመርመርና ንስሐ በመግባት ሥራዓቱን በብርቱ መረዳት መፈጸም ይገባናል።

# ጥናት ሃያ አንድ
# 1ኛ ቆሮንቶስ፡- 12:1-14:40
# አጠቃላይ መግቢያ
# ክፍል 1 - መንፈሳዊ ስጦታዎች

**ዓላማ፡-**

በጋራ አምልኮ ወቅት የቅዱሳንን ኅብረት የሚመዝን በፍቅር የታነጸ መንፈሳዊነትና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን አጠቃቀም አግባባዊ በሆነ መልኩ ለማስገንዘብ

**መግቢያ፡-**

ይህ ክፍል በአማኞች መካከል የመንፈስ ቅዱስን አሠራር በተመለከተ የነበረን አንዳንድ የተሳሳተ መረዳት ለማስተካከል የተሰጠ ጥልቅ ምክር ነው። ክፍሉ እኛንም የሚመለከት ነው። ለመንፈስ ቅዱስ አሠራር የተመቸን እንድንሆን፣ የኅብረታችንና የግላችንን መንፈሳዊ ልምምድ ጤናማ ለማድረግ ይህን ክፍል በትጋት ልንመረምር ይገባል። ገላ 5:25 እንደዚህ የሚል መልዕክት እናገኛለን ። "በመንፈስ የምንኖር ከሆን በመንፈስ እንመላለስ" በመንፈስ መመላለስ ማለት ግን ምን ማለት ነው? በመንፈስ መመላለስ ማለት ለመንፈስ ቅዱስ ራስን (ባሕሪን) ማስገዛት ማለት ነው። ለጸጋ ስጦታዎች አሰራር አዛገቱና መሪው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ አደራረጉም ሆነ ስርዓቱ እንደ መነፈስ ፈቃድ እንጂ በፍጹም እንደ አገልጋዩ ፍላጎትና አሰራር እንዳልሆነ ግልጽ የሚያደርግ ክፍል ነው።

በግምባር ቀደምትነት ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆር 12-14 ያሉትን ሶስት ምዕራፎች የጻፈበት ምክንያት ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የመንፈሳዊነትን ትርጉም እንዲረዱ ለማስገንዘብ እንደሆነ እንረዳለን። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ከተከተሉት መሪ አኳያ ተነስተው እኔ እበልጣለሁ፣ እኔ እበልጣለሁ የሚል አዝማሚያ እንደነበራቸው (1ቆሮ 1-4) ፣ ሌሎቹ ካላቸው የታላቅነት ስሜት የተነሳ ለጣኦት የታረደ ስጋ እንኳን ለመብላት ነጻ እንደሆኑ (1ቆሮ 8-10) ሲያስቡ በ1ቆር 12-14 መሰረት ደግሞ በልሳን በመናገራቸው ከማይናገሩት እንደሚበልጡ ያስቡ እንደነበር እንገነዘባለን።

በመቀጠልም በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ለክርስቶስ አካል ስለተሰጡትና በጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ስለነበሩት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ተናግሮአል። ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባትና ለመቀደስ ታስበው የተሰጡት እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ልዩ ልዩና መንፈስ ቅዱስን ገላጮች ናቸው። እነዚህ ስጦታዎች በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት እጅግ አስፈላጊ እንደነበሩ ሁሉ በዛሬዋም ቤተ ክርስቲያን ጌታ ዳግም እስከሚመጣበት ድረስ ሳይቋረጡ በአገልግሎት ውስጥ እንዲገለጡ ተመልክቷል (1ቆሮ. 1:7) ።

በምዕራፍ 12 ለተጠቀሱ የጸጋ ሥጦታዎች የምዕራፍ 13 ፍቅር በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ያስተምራል። በተጨማሪም 1ቆሮ 14 በተለይም በቆሮንቶስ ቤ/ክ አማኞች ምዕራፍ 12 ላይ የተጠቀሱ ስጦታዎችን እንደሚገባ ለመጠቀም ሥነ ሥርዓት ወይም አንዱ ለአንዱ መገዛት ጠቃሚ ነው ብሎ ያስተምራል።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በመግቢያው መሰረት ሶስቱን የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ችግር በማብራራት ተወያዩ
2. በ1ቆሮ. 12-14 መሰረት ለአንድ ክርስቲያን ከመንፋሳዊ ስጦታዎች በፊት ምን ያስፈልገዋል ይላሉ?
3. የመንፋሳዊ ስጦታዎችን በአግባቡ ለመጠቀም በግምባር ቀደምትነት ምን ይጠበቅብናል (ገላ. 5:25)
4. በ1ቆሮ.12-14 (ሶስቱ ምዕራፎች) የምንገነዘበው ምንድን ነው?
5. የመንፈሳዊ ስጦታዎች ምንጭ ማን ነው (1ቆሮ. 12:11)?
6. የመንፋሳዊ ስጦታዎችን አንድነትና ልዩነት (ዓላማና ዝርዝር) ያብራሩ?
7. ባሕሪን ለመንፈስ ቅዱስ አስገዝቶ እንደ ፈቃዱ መኖርና ማድረግ ምን የሚባል ስያሜ አለው (ገላ. 5:25)? ምንስ ጥቅም አለው?
8. እግዚአብሔርንና ሰውን ስንወድ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ምን ያደርጋል (1ቆሮ. 13:1-3)?

9. የ1ኛ ቆሮንቶስ 12፥13 እና 14 ግንኙነታቸውን አብራሩ።

10. በአሁኑ ዘመን በቤ/ክን ውስጥ ያለው ችግር ምንድ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? መወቃቀስ እና መወነጃጀል ሳይኖር ተወያዩ።

## መደምደሚያ

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ሕግ መሰረት ለእግዚአብሔርና ለሰው ማለትም ወደ ላይና ወደ ጎን ፍቅር ካለን መንፈስ ቅዱስ በስጦታዎቹ አማካኝነት ዘላለማዊ ፍሬ ለመስጠት ይሰራል። መንፈሳዊ ስጦታዎችንም ሆነ ምንጫቸውን እንዲሁም የአጠቃቀማቸውን ሥርዓት በማወቅም ፍሬ እያፈራን ለሰው ጥቅምና ለጌታ ክብር እንኖራለን።

## ጥናት ሃያ ሁለት
## 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12:1-11
## ክፍል 2 - የመንፈሳዊ ስጦታዎች ምንጭ

**ዓላማ፡-**

ለእያንዳንዱ አማኝ የሚሰጡት የተለያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ባለቤትና ምንጭ እግዚአብሔር መሆኑን ማስገንዘብ

**መግቢያ፡-**

ሐዋርያው ይህንን ምዕራፍ የጻፈው ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች እንዲያውቁ ነው (1ቆሮ 12:1)። የቆሮንቶስ አማኞች የነበረባቸው አንዱ ችግር ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና አጠቃቀማቸው እውቀት ማጣት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለመግለጽ የሚጠቀምባቸው ቃላት ወሳኝ ናቸው። ስለሆነም መንፈሳዊ (ኑማቲክ) የሚለው ቃል ኑማ (መንፈስ) የሚለውን መንፈስን ሲያመለክት፣ ካሪስማታ (የጸጋ ስጦታዎች) የሚለው ደግሞ ስጦታን ያመለክታል። ስለሆነም የእነዚህ ሁለት ቃላት ጥምረት የስጦታዎቹ ባለቤት ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያመለክታል። ከዚህ እውነታ በመነሳት ሐዋርያው ጳውሎስ አንድን ክርስቲያን መንፈሳዊ የሚያደርገው ከሁሉ በፊት ጌታ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ያስገነዝባል (1ቆሮ. 12:1-3) ። መንፈስም በቤተ ክርስቲያን ራሱን በልሳን ተናጋሪዎች ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ ስጦታዎች አማካኝነት እንደሚገልጽ ተዘርዝሯል (1ቆሮ. 12:4-11) ።

ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተከሰቱት መንፈሳዊ ስጦታዎች ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑን፣ የስጦታዎቹን ልዩ-ልዩነትና የአጠቃቀማቸውን ይዘት፣ እንደዚሁም የመንፈስ ቅዱስ በሰዎች ላይ መውረድ ክርስትናን ለማስፋፋትና ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ እንደሆነ ይገልጻል (1ቆሮ. 12:1-11)

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ስለነበሩትና ለክርስቶስ አካልም ስለተሰጡት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ተናግሮናል። የስጦታዎቹም ባለቤት እግዚአብሔር እነዚህን ስጦታዎች ጌታ ኢየሱስ እስከሚመጣበት ድረስ ሳይቋረጡ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ እንዲገለጡ የወሰነ ሲሆን እነዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚሰጡት

ቤተ ክርስቲያንን ለማሳደግና ለማነጽ እንጂ ለግል ጥቅምና ክበር እንዳልሆነ መገንዘብ አጽንኦት ተደርጎበታል።

**የመወያያ ጥያቄዎች (1ኛቆሮ. 12:1-11)**

1. በመግቢያው መሰረት የኑማና(የመንፈስ)የካሪስማታ (የጸጋ ስጦታዎች) ጥምረት ማንን ያመለክታል?
2. "ስለ መንፈሳዊ ነገርም፥ ወንድሞች ሆይ፥ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ "(1ቆሮ:- 12:1) የሚለው አባባል ምን ማለት ነው? ስለ ቆሮንቶስ ቤ/ክን ምንን ያሳያል፣ የሚከተሉትን ጥቆሶች በማንበብ አመሳክሩ መዝ 115:5; መዝ 135:15; ዕንባ 2:18-19።
3. የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አማኞች በዓለማዊ ሕይወታቸው ያመለኳቸውን "ድምጽ የሌላቸው ጣዖታት" የተባሉትን ያብራሩ (1ቆሮ:- 12 :2)። በከተማው የተበሩትን ጠዖታትን በባለፈው ጥናት አጥንተናል።
4. በእግዚአብሔር መንፈስ የሚናገር ኢየሱስ የተረገመ ነው እንደማይል ሁሉ በመንፈስ የተወለደ ካልሆነም በስተቀር ኢየሱስ ጌታ ነው ማለት አይችልም (1ቆሮ. 12:3) ይህንን መልዕክት ያስረዱ። በከተማው ከባድ የጣዖት አምልኮ እንደነበር አትርሱ።
5. 1ቆሮ. 12:4-6 "የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው" የሚሉትን ተንትነው ያስረዱ
6. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የሚገለጥባቸውን መንገዶች (1ቆሮ. 12:7-11) ይዘርዝሩ
7. የሚከተሉትን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በራስዎ አገላለጽ በአጭሩ ያስረዱ
   - ጥበብን መናገር
   - እውቀትን መናገር
   - እምነት
   - የመፈወስ ስጦታ
   - ተዓምራትን ማድረግ

- ትንቢትን መናገር
- መናፍስትን መለየት
- በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር
- በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም

8. ከሮሜ 12:1-8 ጋር ምን ግንኙነት አለው።
9. ከዛሬ ጥናት ምን ትምህርት አገኘን። እናካፍል።

***መደምደሚያ***

ለማጠቃለል ያህል እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ሁሉ የጌታ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሲሆኑ ለእያንዳንዱ ሰው ጌታ መንፈስ እንደ ፈቀደ ይሰጠዋል (1ቆሮ:-12:11):: እናም እውነታውን ስንመለከት በመንፈስ ቅዱስ ፍላጎት እንጂ በእኛ ምርጫ የምናገኘው ስጦታ አይኖርም። የስጦታዎች ሁሉ ምንጭ የሆነው አንዱ መንፈስ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ምዕመናንን ለማበረታታትና ቤተ ክርስቲያንን ለማስፋፋት ለአማኞች ያድላል።

## ጥናት ሃያ ሶስት
## ፲ኛ ቆሮንቶስ:- 12:12-31
## ክፍል 3 - የመንፈስ ስጦታዎች አንድነትና ልዩ ልዩነት

**ዓላማ**

ልዩ ልዩ የሆኑትን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በተለያዩ የአካል ብልቶች በማመሳሰል የስጦታዎቹን አንድነትና ልዩነት ለመግለጽ

**መግቢያ**

የአካል ብልቶች ልዩ ልዩ አገልግሎት ቢኖራቸውም እንኳን አካሉ በጤናማነት ይንቀሳቀስ ዘንድ የሁሉም ተሳትፎ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ በአማኞች ሕይወት በልዩ ልዩ አሰራሩ የሚሰራው የመንፈስ ቅዱስ አደራረግም ወሳኝ ነው። በዚህም መሰረት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንደሆነችና አባላቶቿም ለመታነፂ በረከት በሆኑ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች የተገነቡ እንደሆኑ ታትቷል (1**ቆሮ.**12:27-30)።

አሳቡን ለማስረዳት ሐዋርያው ጳውሎስ አካልንና ብልቶችን በምሳሌነት ይጠቀማል። የሰው አካል አንድ ሲሆን በዚያው ባንዱ አካል ውስጥ የሚገኙት ብልቶች ብዙ ናቸው። የአንዱ ብልት ደስታም ሆነ ስቃይ ለሌላዎቹ እንደሚተርፍ በ1ቆሮ:- 12:26 ላይ እንመለከታለን። "... ክርስቶስም እንደዚሁ ነው..." (1ቆሮ:- 12:12) በሚለው አባባል ሐዋርያው ጳውሎስ የሰውን አካል በመጠቀም በቤተ ክርስቲያን ባሉ አማኞች መካከል ሊኖር የሚገባውን ህብረት ያስረዳል (ኤፌ:- 2:21፣ 4:16)::

"... እግዚአብሔር እንደወደደ እያንዳንዱን በየቦታው መድቦአል..." (1ቆሮ: 12:18) እያንዳንዱ በቤተ ክርስቲያን የሚገኝ አማኝ የአገልግሎት ድርሻ እንደተሰጠው የሚያመለክት ነው። ይህንም ያደረገው በአካል ብልቶች መካከል መለያየት ሳይኖር እርስ በርሳቸው እኩል እንድተሳሰቡ ነው (1ቆሮ. 12:25) :: በዚህ ጥቅስ መሰረት እግዚአብሔር መንፈሳዊ ስጦታን የሰጠው ለሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት ጥቅም እንደሆነ እንረዳለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች** (፲ኛ **ቆሮ.** 12:12-31)

1. በመግቢያው መሰረት የመንፈስ ስጦታዎችን ልዩነትና አንድነት ተወያዩ
2. ብልቶቻችን የአንድ አካል ክፍል እንደመሆናቸው ሁሉ እኛስ ሁላችን የአንድ አካል ብልት አባል ልንሆን የቻልነው እንዴት ነው (1ቆሮ. 12:12-14)?

3. አካል የብዙ ብልቶች ስብስብ መሆኑን (1ቆሮ. 12:14-16) በዝርዝር ተነጋገሩ:: መንፈሳዊ ምሳሌነቱስ ምንድን ነው?
4. “ሁሉም አንድ ብልት ቢሆንስ አካል ወዴት በሆነ” (1ቆሮ. 12:19) የሚለውን ሐረግ እንዴት ይረዱታል? ከቤ/ክ አባላት ጋር አገናኙ።
5. 1ቆሮ. 12:22-24:- “... ደካሞች የሚመስሉ፣ ያልከበሩ የሚመስሉ፣ የምናፍርባቸው ብልቶች...” ተብለው የተገለጹትን ዐረፍተ ነገሮች ያብራሩ
6. እግዚአብሔር ስለጎደለው ብልት የሚበልጥ ክብር እየሰጠ (1ቆሮ 12:24-25) አካልን የማገጣጠሙ ዓላማ ለምንድን ነው?
7. በ1ቆሮ. 12:31 “...የሚበልጠው የጸጋ ስጦታ...” የተባለው ምን ይመስለዎታል?
8. እንደ ክርስቶስ አካል ብልትነታችን (1ቆሮ. 12:27-31) በቤተ ክርስቲያን ምን ምን አገልግሎት ሊኖረን ይችላል? አሁን ለእርሶ በባሉበት አጥቢያ ቤ/ክ ምን አገልግሎት አልዎት? (ምንም ካሉ ቤ/ክ አገልጋዮችን ያነጋግሩ)

**መደምደሚያ**

የሰው አካል ብዙ ብልቶች ቢኖሩትም አንድ ሰው ተብሎ ይጠራል። እንደዚሁም ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ብዙ አባሎች ሲኖሯት በክርስቶስ አንድ ናት። የሰውነት ክፍሎችም እርስ በእርስ እንደሚረዳዱ ሁሉ አማኞችም መረዳዳት አለባቸው። የስጦታዎቹም አገልግሎት ለአንዱ ለክርስቶስ አካል ነው። ሰጪውም እግዚአብሔር ነው። የአካል ብልቶች ሁሉም አገልግሎት እንዳለባቸው እያንዳንዳችን አገልግሎት ልኖረን ይገባል።

# ጥናት ሃያ አራት
# 1ኛ ቆሮንቶስ:- 13:1-13
# ፍቅር - በቅዱሳን ሕብረት የላቀው ስጦታና መያያዣ

**ዓላማ:-**

ፍቅር ከሁሉ የሚበልጥ ስጦታ በመሆኑ መንፈሳዊ ስጦታዎችን በፍቅር መፈጸም እንዳለብን ለማስገንዘብ

**መግቢያ:-**

መንፈሳዊ ስጦታዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስፈጸም እንዲችሉ የሚገዙበት መርሕ ፍቅር ብቻ መሆን አለበት። በሌላ አነጋገር አንድ አማኝ ፍቅር ሳይኖረው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ባለቤት ቢሆን ምንም እንደማይጠቅምለት ምዕራፍ 13 በግልጽና በዝርዝር ያስረዳል።

በእውነት በመንፈሳዊ ስጦታዎች የሚያገለግል መንፈሳዊ ሰው ከሌሎች ጋር መልካም ግኑኙነትን የሚጠብቅና በመልካም ጠባይም ይሁን ባሕሪ የተሞላ ነው (1ቆሮ:- 13:4-8):: ከቋንቋ አኳያ በሰዎችና በመላዕክት ልሳን ብንናገር (1ቆሮ:- 13:1 )፣ ከስጦታ አኳያ ያለንን ንብረት ሁሉ ብንሰጥ (1ቆሮ:- 13:3)፣ ያለ ፍቅር ከንቱ እንደሆነ እንገነዘባለን። በ1ቆሮ:- 13:4-7 የተገለጹት አያሌ የፍቅር ገጽታዎች የእግዚአብሔር አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ባሕሪ ያሳያሉ። ፍቅር ሙሉ በሙሉ የሚረዳን (1ቆሮ:- 13:12)፣ ፍቅር የሆነውን ራሱን እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ስናየው እንደሆነ ቢታወቅም አሁንም በመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን በፈሰሰው ፍቅር አማካኝነት እየተመላለስን በጸጋ ስጦታዎች ጌታን ልናገለግል ይገባል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. 1ቆሮ 12:31ን በማንበብ የተገበዘባችሁትን ተነጋገሩ።
2. “ፍቅር ግን ከሌለኝ” (1ቆሮ 13:1) የሚለውን መልዕክት እንዴት ይገልጹታል? “...ከንቱ ነኝ...” (1ቆሮ. 13:2) ሲልስ ምን ማለቱ ነው?
3. በ1ቆሮ. 13:1-3 መሠረት የፍቅርን ጥልቀትና ብልጫ እንዴት ይገነዘቡታል)?
4. በ1ቆሮ 13፡4-7 የተገለጹትን የፍቅር ባህርያት ያብራሩ።

- ይታገሳል
- ቸርነት ያደርጋል
- አይቀናም
- አይመካም
- አይታበይም
- የማይገባውን አያደርግም
- የራሱን አይፈልግም
- አይበሳጭም
- በደልን አይቆጥርም
- ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል በአመጻ ግን ደስ አይሰኝም
  የእርሶስ ችግር የቱ ጋ ነው?

5. ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም (1ቆሮ፡- 13:8) ሲል ምን ማለት ነው?
6. የጸጋ ስጦታዎች የሚሻሩት መቼ ነው (1ቆሮ፡- 13:10-11)?
7. ከዕምነት፣ ተስፋና ፍቅር የሚበልጠው ማን ነው እንዴት (1ቆሮ፡- 13:13?
8. በ1ቆሮ 13 ምዕራፍ መሠረት በጸጋ ስጦታ የሚያገለግሉ አገልጋዮች ወይም ቤ/ክ ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።
9. የጸጋ ስጦታዎችና የመንፈስ ፍሬዎች ግንኙነት አላቸው?

***መደምደሚያ***

ምንም ዓይነት የጸጋ ስጦታ ያለ ፍቅር አይበጅም። ይህ የሚሆነው ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ ነው። በሌላ በኩል በልባችን ውስጥ ፍቅር ካለ የእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ የእኔ ሊሆን ይችላል።

## ጥናት ሃያ አምስት
## 1ኛ ቆሮንቶስ:- 14:1-25
## ክፍል 1 - ጉባኤን የሚያንጽ የስጦታዎች አጠቃቀም መመሪያ

**ዓላማ:-**

የክርስቶስን አካል ለማነጽ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ከልብ መሻትና መፈለግ እንደሚኖርብን፣ ስጦታዎቹንም በሥርዓት በጉባዔ መካከል መጠቀም እንዳለብን ለማስገንዘብ

**መግቢያ:-**

ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ስጦታዎች በሙሉ ጉባኤውን ለማነጽና ለማሳደግ እንጅ ላንድ ግለሰብ ወይም ለተወሰነ ቡድን የሚለገሱ እንዳልሆኑና የግለሰቡም ይሁን የቡድኑ መንፈሳዊነት መለኪያ እንዳልሆኑ በአንክሮ የሚያሳይ ምዕራፍ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ከመንፈሳዊ ስጦታዎች በይበልጥ ትንቢትን የመናገር ስጦታን በብርቱ መፈለግ እንዳለባቸው አበክሮ ይነግራቸዋል።

ሌሎችን በመምከር በማጽናናትና በማበረታታት ለማገልገል የሚረዱ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለማግኘት በትጋት መሻት፣ መፈለግና መጸለይ ያስፈልጋል (1ቆሮ 14:1,12):: የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጉባኤ አምልኮ ውስጥ የልሳን ስጦታን አስፈላጊነት ከሚገባ በላይ በማጋነን ከሌሎች ስጦታዎች ይልቅ ትኩረት እንዲያገኝ ያደርጉ ነበር (1ቆሮ:- 14:1-12)። ከዚህም በላይ ይህንን ስጦታ ሳይተረጎም ይጠቀሙበት ነበር (1ቆሮ:- 14:1-5)። ሊተረጎምና ሊታወቅ የማይችል ከሆነ ደግሞ አካሉን ሊያንጽ እንደማይችል ሐዋርያው ያብራራል።

ካልተተረጎመ ልሳን ይልቅ ትንቢት ቤተ ክርስቲያንን እንደሚያንጽ (1ቆሮ:- 14:1-4)
"… ራሱ ይባረካል…" (1ቆሮ:- 14:2፣ 6-11) በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገር ራሱ ይባረካል እንጂ ሌሎች ሊያስተውሉት አይችሉም።
"… ትንቢት የሚናገር…" (1ቆሮ:- 14:3) ሁሉም ስለሚሰሙት ይጠቀሙበታል።

ትንቢታና የተተረጎመ ልሳን ለቤተ ክርስቲያን እኩል አስፈላጊ እንደሆኑ (1ቆሮ:- 14:5)

ያልተተረጎመ ልሳን በጉባኤ አገልግሎት ውስጥ ለሌሎች ምንም ጥቅም እንደሌለው (1ቆሮ:- 14:6-12)

“… ካልተተረጎመ መተርጎም እንዲችል…” (1ቆሮ:- 14:3፣ 13) የቋንቋ ጥቅሙ አንዱ ሲናገር ሌላው የተረዳ እንደሆነ ብቻ ነው። አንዱ በልዩ ቋንቋ ሲናገር አስተርጓሚ ካልኖረ ለሌሎች ጥቅም አይሆንም።

በጉባኤ በልሳን የሚናገሩ ቤተ ክርስቲያንን ያንጹ ዘንድ የመተርጎም ስጦታ እንዲሰጣቸው መጸለይ እንዳለባቸው (1ቆሮ:- 14:13)

በሐዋርያው ጳውሎስ የግል ሕይወት ውስጥ በልሳን ለእግዚአብሔር መናገር ለ አምልኮና ለመንፈሳዊ ዕድገት መምገድ በመሆን ጠቃሚነቱ የጎላ እንደነበር (1ቆሮ:- 14:14-19)

ሃጠተኛነትን ለመረዳትና የእግዚአብሔርን ሀልዎት ለማወቅ ስለሚያግዝ ካልተተረጎመ ልሳን ይልቅ ትንቢት እንደሚጠቅም (1ቆሮ:- 14:20-25)

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉ በስር አት ይሆን ዘንድ ትንቢትን መናገርና በልሳን መጸለይ በ አግባቡ መደረግ እንዳለበት 1(ቆሮ:- 14:26-40)

## የመወያያ ጥያቄዎች (1ቆሮ. 14:1-25)

1. 1ቆሮ. ምዕ. 14 ከ12 እና 13 ጋር ምን ግንኙነት አለው? ተወያይ
2. በ1ቆሮ. 14:1 ላይ “ፍቅርን ተከታተሉ” ሲል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?
3. በልሳን የመናገር ጥቅም ምንድን ነው (1ቆሮ. 14:1-5)?
4. 1ቆሮ. 14:1-5 መሰረት በጉባኤ መካከል በልሳን ከመናገር በትንቢት መናገር ትኩረት የተሰጠው ለምንድን ነው?
5. ዋሺንት፣ ክራርና መለከትን (1ቆሮ.14:7-8) ሐዋርያው ጳውሎስ ምንን ለማብራራት ነው የተጠቀመባቸው?
6. 1ቆሮ. 14:1፣12 መሰረት ትንቢት መናገርን በብርቱ የምንፈልግበት ዓላማው ምንድን ነው?
7. በመንፈስና በዓዕምሮ የመጸለይን (1ቆሮ.14:15-16) ልዩነት ያብራሩ

8. ሐዋርያው ጳውሎስ እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአዕምሮ መናገርን የመረጠበት ምክንያቱ ምንድን ነው (፲ቆሮ. 14:19)?
9. ፲ቆሮ.14:6-9 መሠረት የሚታወቀውን ቃላት በአንደበት ባንናገር ለነፋስ እንደምንናገር የተመሰለው ለምንድን ነው?
10. ሕጻናት መሆን የሌለብንና ያለብን ለምን ጉዳይ ነው (፲ቆሮ. 14:20)?
11. በልሳን መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው ሲል ምን ማለት ነው (፲ቆሮ. 14:22)?
12. በጉባኤ መካከል ከእግዚአብሔር የሆነ ትንቢት በብዙዎች ቢነገርና የማያምኑ ሰዎች ቢገኙ ጥቅሙ ምንድን ነው (፲ቆሮ. 14:25)
13. ከዛሬው ጥናት ምን ተረዳችሁ? ተወያዩ።

## መደምደሚያ

በጥቅሉ በጉባኤ መካከል ትንቢት እየተነገረ ባለበት ወቅት የማያምን እንግዳ ሰው ቢገባ በሁሉም እንደሚመረመር፣ እንደሚወቀስ፣ በልቡ ያለውና የተሰወረውም ነገር ተገልጦ በእርግጥ እግዚአብሔር በመካከላቸው ነው በማለት በግንባሩ ተደፍቶ ለእግዚአብሔር እንደሚሰግድ (1ቆሮ:- 14:25) ይህ ክፍል ያስረዳል። የመንፈስ ስጦታም አንዱ ጥቅሙ ሰዎችን ወደ ጌታ ማምጣት እንደሆነ ይህ ጥናት ያስተምረናል።

## ጥናት ሃያ ስድስት
## 1ኛ ቆሮንቶስ:- 14:26-40
## ክፍል 2 - መንፈሳዊ ስጦታዎችን በስርዓቱ መጠቀም

**ዓላማ፡-**

እግዚአብሔር አምላካችን የሥርዓት አምላክ በመሆኑ የሰጠንን መንፈሳዊ ስጦታዎችም በሥርዓትና በአግባቡ መጠቀም እንደሚኖርብን ለማስገንዘብ

**መግቢያ፡-**

ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ስጦታዎችን በምንጠቀምበት ጊዜ ሥርዓት ባለው መንገድና በተራ እርስ በእርስም በመደማመጥ ሊሆን እንደሚገባው በደንብ በማብራራት የተገለጸበት ሰፋ ያለ ክፍል ሲሆን ፣ የዚህም መነሻ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበረው የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀም ሥርዓት-አልበኝነት እንደሆነ በስፋት ተዳስሷል።

የመንፈሳዊ ስጦታዎች ሁሉ ዋና ዓላማ ቤተ ክርስቲያንንና ግለ ሰቦችን ማነጽ ነው። ማነጽ ማለት ደግሞ በአማኞች ውስጥ መንፈሳዊ ሕይወትን፣ ብስለትንና የቅድስናን ባሕሪ ማሳደግ ነው። አማኞች ይህንን ዓለም ሳይመስሉ (ሮሜ. 12፡2-8) በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አማካኝነት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በይበልጥ እየተለወጡ በቅድስና፣ እግዚአብሔርን በመውደድ፣ ስለ ሌሎች በማሰብ፣ በልብ ንጽህና፣ በንጹህ ህሊናና በእውነተኛ እምነት እንዲያድጉ የሚያደርጋቸው መንፈስ ቅዱስ ነው (ሮሜ. 8:13፣ ኤፌ. 2:19-22፣ 1ተሰ:- 5:11)

**ማብራሪያ**

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል በሚከተለው መልኩ ስርዓታዊ አጠቃቀምን አስቀምጧል።

"… ከሁለትና ከሶስት… በተራ…" (1ቆሮ:- 14:27):- በጉባኤ መካከል ከሁለትና ከሶስት የበለጠ በልሳን ጮኾ ብሎ መናገርየለበትም፤ ተርጓሚም እንኳ ቢኖር ተራ በተራ እንጂ ሁሉም ባንድነት መናገር የለበትም።

1ቆሮ:- 14:26-28 - ተርጓሚ ይኑር

የጉባኤ አገልግሎት አማኞች እርስ በርስ የሚተናነጹበት ጊዜ በመሆኑ ልሳን በሚነገርበት ወቅት ራሱ ተናጋሪው ወይም ሌላ የመተርጎም ስጦታ ያለው ሰው ሊተረጉም ያስፈልጋል።

"... ሁለት ወይም ሶስት ነቢያት..." (1ቆሮ:- 14:29) በጉባኤ ከካከል ትንቢት ተናጋሪዎች በተራ በተራ ይናገሩ፣ ሌሎችም የተባለውን ያዳምጡና ይመዝኑ።

1ቆሮ:- 14:29-33 ስርዓት ይጠበቅ

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን የተናገረው አንዱ ልሳን በሚናገርበት ወቅት ሌላው ድምጹን ከፍ አድርጎ ይሸኛውን በማቋረጥ በልሳን ይናገር እንደነበር ይታመና። በዚህም ምክኛት ሐዋርያው የነቢያት መናፍስት ለነቢያት ይታዘዛል በማለት ያሳስባል። ስለሆነም የጉባኤው መንፈስ በመልካም ሁኔታና በስርዓት መሆን እንደሚኖርበት ይህ ክፍል ያስረዳል።

1ቆሮ:- 14:- 34-36 - ሁከት አይኑር

ሴቶች በጉባኤ ዝም ይበሉ የሚለው አባባል በ አውዱ መሰረት የሴቶች ድምጽ ልሳንን በማስተጋባት በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎቹ የባሰበት እንደነበረ ብዙዎች ይስማሙበታል።

1ቆሮ:- 14:37-40 - ልሳን መናገር አልተከለከለም

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ሊያስተላልፍ የፈለገው የልሳን ስጦታ ከሌሎቹ ሁሉ የበለጠ እንዳልሆነና ተርጓሚ ከለለም ጉባኤውን ለማነጽ ጭብጥ ነገር ስለማይገኝበት ለመተርጎም መጸለይ እንደሚያስፈልግ ነው።

እንደ መደምደሚያም:- "... ትንቢት ለመናገር በብርቱ ፈልጉ፣ በልሳን መናገርንም አትከልክሉ ነገር ግን ሁሉም በ አግባብና በስርዓትይሁን" (1 ቆሮ:- 14:40) በማለት ያጠቃልላል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የ1ቆሮ.14 ዋና መልዕክት ምንድ ነው?
2. በ1ቆሮ.14:26 መሰረት በጉባኤ ስንሰበሰብ ስርዓቱ መሆን ያለበት እንዴት ነው?
3. በልሳን የመናገርና በትንቢት የመናገር ሥርዓት (1ቆሮ:- 14:27-31) መሆን ያለበት እንዴት ነው?
4. በጉባኤ ትንቢት የመናገር (1ቆሮ.14:31) ዓላማው ምንድን ነው?

5. 1ቆሮ.14:32-33 ያለውን መልዕክት ያስረዱ
6. ሐዋርያው ጳውሎስ 1ቆሮ.14:14ን "ይህች የጻፋችሁልኝ የጌታ ትዕዛዝ እንደሆነች…" ያለውን በዝርዝር ያስረዱ
7. ትንቢት የመናገርም ሆነ ልሳን የመናገር ወጉ ወይም ሥርዓት (1ቆሮ. 14:39-40) ምንድን ነው?
8. ማንም ማንንም ሳይወቅስ ወይም ስም ሳይጠራ የአሁን ቤ/ክ ችግሯ ምንድ ነው? ምን ይደረግ? እኛስ ባለንበት የአገልግሎት ዘርፎች ታዛዦች ነን?
9. ዛሬ ለጸጋ ሥጦታዎችና ለሥርዓት እንጸልይ። ተባረኩ!

**መደምደሚያ**

እግዚአብሔር አምላክ የሥርዓት አምላክ እንደሆነ ሁሉ እኛም በሥርዓት መኖርና ማገልገል ይጠበቅብናል። ለአንድ ሰው መንፈስ ቅዱስ መልዕክት ሲሰጠው እርሱ ሳይጨርስ ሌላው አይጀምር፤ የነቢያት መናፍስት ለነቢያት ይገዛሉና ተራውን ይጠብቅ።

# ጥናት ሃያ ሰባት
# 1 ቆሮንቶስ ም ዕራፍ 15:1-11
# ክፍል ፩ - የክርስቶስ ትንሳኤ

***ዓላማ፡-***

***የክርስቶስ ትንሳኤ በእውነትና በእምነት ላይ መመሥረቱን ማሳየት***

***መግቢያ፡-***

፩ቆሮንቶስ መልዕክት በቆሮንቶስ አማኞች መካከል የነበሩትን ልዩ ልዩ ችግሮችን (የሥነ ምግባር፣ ሥነ ሥራአትና የሀሰት ትምህርቶችን)የዳሰሰ እንደሆነ ተመልክተናል። ይህንንም ያርማል፣በእውነተኛ የክርስትና ትምህርት ላይ የሚነሱትንም የሀሰት ትምህርቶችን በመቃወም እውነተኛውን ትምህርት ያስተምራል።

ከእነዚህም በመጀመሪያ መቶዎቹ ዓመተ ምህረት ከነበሩት የስህተት ትምህርቶች አንዱ ስለ ክርስቶስና ስለ አማኞች ትንሳኤ ይሰጥ የነበረ የሀሰት ትምህርት ነበር። ማለትም ትንሳኤ ሙታን የለም ወይም ከዚህ በፊት ሆኖ ያለፈ ነገር ነው ብለው የሚያስተምሩ ነበሩ። ሌሎች ደግሞ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ያወሩት የውሸት ወሬ እንጂ በትክክሉ ክርስቶስ አልተነሳም ይሉ ነበር። እንዳውም አንዳንዶች ኢየሱስ ክርስቶስን የሚመስል ሰው ተሰቀሎ ሞተ እንጂ እርሱ አልሞተም ይሉም ነበር። ሌሎች ደግሞ እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ አካል መልበስ የማይሆን ነገር ነው ይሉ ነበር። ከእነዚህም ሌላ ከአይሁድ የኃይማኖት ክፍሎች አንዱ የሆነው የሳዱቃውያን ትምህርት ትንሳዔ እንዳለ አያምንም ነበር (ማቴ 22፡23 ሐዋ 23:7-9)። በዚህ ምክንያት ሐዋርያው ጳውሎስ የተስሎንቄን መልዕክት፣ ፩ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ፲፭ን እና ሌሎችንም ጻፋቸው።

ስለዚህም ፩ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ፲፭ በዋናነት በበቂ ማስረጃ የሚያስተምረን ስለ ክርስቶስ እና ስለ አማኞች የሙታን ትንሳኤ እውነተኛነት ነው። በዚህም መሠረት ከዚህ ምዕራፍ ሶስት ጥናቶችን እናያለን። ከቁ.1-11 የመጀመሪያ፣ ከቁ.12-34 ሁለተኛው ሲሆን ከቁ.35-58 ሶስተኛው ጥናት ይሆናል።

በዚህ በመጀመሪያ ክፍል ጥናት ማለትም ፩ቆሮ.፲፭፡፩-፲፩ ባሉት ቁጥሮች ሐዋርያው ጳውሎስ ለማንኛውም ነገር የጌታ ትንሳኤ መሠረት እንደሆነ ያስረዳል።

ያለ ክርስቶስ ትንሣኤ የክርስትና እምነት ዋጋ የሌለው የሰው ፍልስፍና ብቻ ሆኖ ይቀራል። ትንሳኤ ከቤተ ክርስቲያን አስተምሮሆች አንዱ ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ለማስታወስ ያህል በቆሮንቶስ አማኞች መካከል የነበሩትን ልዩ ልዩ ችግሮችን ተወያዩ
2. ከመግቢያ ስለ 1ቆሮንቶስ 15:1-58 የተረዳነውን እናካፍል
3. ይህ ምዕራፍ ለመከላከል የፈለገው በወቅቱ የነበረው የስህተት ትምህርት ምን ነበር? ምንስ ያስተምር ነበር?
4. በማቴ.22:23-33 እና ሐዋ.23:8 በማንበብ በክፍሉ የተጠቀሱ ሰዎች ትምህርታቸውና እምነታቸው ምን ነበር?
5. በማቴ.22:32 "'እኔ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ ነኝ።' እግዚአብሔር የሕያዋን እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም" የሚል ቃል ስለ ትንሳኤ ምን ያስተምራል?
6. በ1ቆሮ. 15:1-11 መሰረት ጌታ ከሞት ተነስቶ ለእነማን እንደታየ ተወያዩ? ይህ መሆኑ ምን ይጠቅማል?
7. የ1ቆሮ 15:1-11 ዋና ትምህርት ምንድ ነው?
8. በዚህ ክፍል ጥናት መሠረት ሐዋርያት የሰበኩት እና ጸንተው የቆሙት የክርስቶስ ትንሳኤ ወንጌል ባይኖር የያዝነው ክርስትና ምን ችግር ይገጥመዋል ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?
9. ከዚህ ጥናት የተረዳችሁትን ለጥናቱ አባላት አካፍሉ

## መደምደሚያ

1ቆሮ. ምዕራፍ 15 ስለ ትንሣኤ እጅግ የዳበረ ሥነ-መለኮታዊ ክርክር እና ማስረጃ ነው። ለአማኞች ትንሣኤ ዋናው መሰረት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው። ክርስትና የክርስቶስ ትንሳኤ አስተምህሮ ከለሌው ተስፋ የሌለው በሰው የተፈጠራ ፍልስፍና ሆኖ ብቻ ይቀራል። በትንሳዔ ትምርት ጸንተን መቆምና ለሌሎችም ማወጅ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው።

## ጥናት ሃያ ስምንት

## 1 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15:12-34

## ክፍል 2 - የሙታን ትንሣኤ እውነተኛነት

**ዓላማ:-**

በባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስ ትንሣዔ በዓይን ምስክሮች የተረጋገጠ መሆኑን አስረግጧል። የዚህ ጥናት ደግሞ ዓላማው የአማኞችም ትንሣኤ የአማኞች ሙሉ ተስፋ እና የተረጋገጠ እውነት እንደሆነ ማስረዳት ነው።

**መግቢያ:-**

በቆሮንቶስ አማኞች መካከል ትንሳዔ ሙታን የለም የሚሉ እንዳሉ በግልጽ 1ቆሮ 15:12 ይናገራል። በዚህ ክፍል የቆሮንቶስ መልዕክት የሚያስተምረው ትንሣኤ ለክርስቶስ ብቻ ሳይሆን የአማኞችም ጭምር መሆኑን ነው። ክርስቶስ የአማኞች ትንሳኤ በኩር መሆኑንም ያስተምራል።

በዚህ ክፍል መሠረት አንዳንዶች ክርስቶስ መነሳቱን አምነው ነገር ግን የአማኞች ትንሳኤ የለም ይሉ ስለነበር ሐዋርያው የእነርሱን አቋምና ትምህርታቸውን ለመቀየር የመከራከሪያ ነጥቦችን እያቀረበ ሲያስተምራቸው እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. 1ቆሮ 15፡12-19 ከቁ.1-11 ካለው ጋር ምን ግንኙነት አለው
2. ይህ ዓለም ሙሉ ሙሉ ለጌታ የሚገዛው መቼ ነው?
3. 1ቆሮ 15:12-19 ሐዋርያው ጳውሎስ ያቀረባቸውን የመከራከሪያ ነጥቦችን ተወያዩ
4. በሰው ልጆች ታሪክ ላይ የአዳምና የክርስቶስ መሪነታቸው በምን እና በምንድ ነው
5. “መገዛት” የሚለውን ቃል በክፍሉ መሠረት አብራሩ።
6. 1ቆሮ 15:29-35 ዋና መልዕክት ምንድ ነው?

7. 1ቆሮ 15:29 መሠረት በቆሮንቶስ ከተማ አንዳንዶች ለሙታን ይጠመቁ የነበሩ ለምንድ ነው? ሐዋርያውስ የእነርሱን ልምምድ በዚህ ክፍል የተጠቀመው ለምንድ ነው?

8. ከወንጌል ስለ አማኞች ትንሣኤ የሚታውቁት ክፍል ካለ ጥቀሱ
9. ይህ ጥናት ለእኛ ለአማኞች እጅግ አስፈላጊ ትምህርት ነው። ለምን እንደሆነ ተወያዩ።

***መደምደሚያ***

ክርስትና የአማኞች ትንሳኤ ከሌለ ሰዎችን ጥሩ ሥነ ምግባር የሚያስተምር የሰዎች ፍልስፍና ወይም ሰው ሰራሽ ኃይማኖት ብቻ ሆኖ ይቀራል። ትንሳኤ ተስፋችን ነው። ትንሳኤ ከክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ጋር እጅግ የተቆራኘ እውነት ነው። ጌታም እንዲህ አለ "ስለ ትንሣኤ ሙታን ግን፦ እኔ የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ የሚል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን? የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም" (ማቴ 22:31-32)።

# ጥናት ሃያ ዘጠኝ
# 1 ቆሮ 15:35-58
# ክፍል 3 - የትንሣኤ አካል

**ዓላማ፦**

በክርስቶስ ያመነ ሰው አማኝ የትንሳኤ አካል እንዳለ በእምነት መቀበል እና ለሌሎችም የትንሳኤን አካል እውነት መመስከር እንዳለበት ማስገንዘብ

**መግቢያ፦**

የሰው ልጅ በምድራዊ እውቀቱ ስለ ብዙ ነገሮች ወይም ፍጥረታት ተንትኖ ማወቅ እንደማይችል ሁሉ የትንሳኤ አካልም በምድራዊ እውቀቱ ሊያብራራ እንደማይችል በማወቅ የአማኝ የትንሣኤ አካል በእምነት በእግዚአብሔር ችሎታ ሊሆን እንደሚችል በማመን መቀበል እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው።

ሙታን የሚነሱ ከሆነ በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ጥያቄ በወቅቱ ከነበሩት አሳሳች ወይም የሥጋ እውቀት ጥያቄዎች አንዱ ነበር። የትንሣኤን አካል በተመለከተ፣ የሚነሣው ጥያቄ በአንዳንድ የግሪክ ፍልስፍና ትምህርት ቤቶች በነበረ በሥጋዊ አካል ላይ ካለ አሉታዊ አተያይ የተነሳ ጥያቄ ነው። አንዳንድ ግሪኮች ዘወትር ቁስ-አካልን (ለምሳሌ ሥጋን) እንደ ክፉ ይመለከቱ ነበር። ሥጋ የንጹህ ነፍስ እስር ቤት ነው ብለውም ይናገራሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ ለእንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል (15፡35-57)። ይህንንም መቀበል የምንችለው በመንፈሳዊ እውቀት ነው ይላል።

ስለዚህ በዚህ ክፍል ሐዋርያው ስለ ትንሳኤ አካል ባህርይ ሲያስረዳ የትንሳኤን አካል ከተክሎች (36-38)፣ከሥጋ ለባሽ ከሆኑ ፍጡራንና (ቁ.39) ከሰማያዊና ምድራዊ አካላት ጋር ያነጻጽራል (40-41)።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. 1ቆሮ 15:35-45 "ሙታን እንዴት ይነሣሉ" የሚሉ ሰዎች ዋናው ችግራቸው ምንድ ነው?

2. የትንሳኤ ሙታንን እውነት ለማስረዳት ሐዋርያው ጳውሎስ የተጠቀማቸው ምሳሌዎች ምን ምንድ ናቸው? ምንስ ያስተምራሉ?
3. 1ቆሮ 15:42-50 በማንበብ በዚህ ክፍል ጸሃፊው የአዳምና የክርስቶስን ምሳሌን ማነጻጸሩ ለምን አስፈለገ?
4. 1ቆሮ 15:42-50 መሠርት ሐዋ ጳውሎስ ስለ ትንሳኤ አካል ለማስተማር የተጠቀማቸው ተቃራኒ ነገሮችን ተወያዩ። እነዚህ ተቃራኒ ነገሮች መጠቀሳቸው ለምን ያስፈልጋል?
5. በ1ቆሮ 15፥51-57 ባለው ክፍል የጌታ ቃል እንደሚነግረን ትንሳኤ መቼ እና እንዴት እንደሚሆን ተወያዩ?
6. በ1ቆሮ 15:35-58 የዚህ ክፍል ጥናት ዋና መልእክት ምንድ ነው? ተወያዩ
7. በ1ቆሮ 15:58 ያለውን ምክር ተወያዩ አሁን ለእኛ ምን ይጠቅማል?
8. በአጠቃላይ ከዚህ ጥናት ምን ተረዳችሁ። ለቡድኑ አካፍሉ።

## መደምደሚያ

የትንሣኤው አካል አዲስ ዓይነት አካል ነው። በሚጠፋ ምትክ የማይጠፋ፣ በተዋረደ ምትክ የከበረ፣ ከደካማ ይልቅ የበረታ፣ ከሥጋዊ ይልቅ መንፈሳዊ እንደሚሆን በዚህ ክፍል ተገልጿል። ስለዚህ ትንሳኤ ሙታን የአማኞች በአካል የሚሆን እውነት ነው።

## ጥናት ሰላሳ
## 1 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 16
## ለወንጌል መስፋት የአብያተ ክርስትያናት መደጋገፍ

**ዓላማ፡-**

ለወንጌል መስፋፋት የአብያተ ክርስትያናት መደጋግፍ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ማስገንዘብ

***መግቢያ***

1ቆሮ 16 እንደምናውቀው የመጨረሻ ምዕራፍ ሲሆን በጥቅሉ ሶስት ነገሮችን ያስተምራል። እነዚህም ሶስቱ ዋና ነገሮች፡- ለወንጌል ሥራ ስለ አብያተ ክርስትያናት በገንዘብ መደጋገፍ (1ቆሮ 16፡1-4) ፤ የሐዋርያውን እቅድ ማስተዋወቅ (1ቆሮ 16፡5-18) እና የመሰናበቻ መልዕክት ናቸው (1ቆሮ 16፡ 19-24)።

**የክፍሉ አጭር ማብራሪያ**

1. **የአብያተ ክርስቲያናት መደጋገፍ፡-**

1ቆሮ 16:1-4 እንደሚያስረዳን ሐዋርያው ጳውሎስ በአካይያ አውራጃ ላለች ለቆሮንቶስ ቤ/ክ የገላትያና የመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት ሌሎችን እንደሚረዱ እነዚህም ለኢየሩሳሌም አማኞች ገንዘብ አሰባስበው እንዲልኩ ይጠይቃቸዋል። ይህ እርዳታ ያስፈለገው እንደሚታወቀው በኢየሩሳሌም የነበሩ አማኞች ራሳቸውን ከአይሁድ ኃይማኖት ከለዩ በኋላ ብዙ ስደት እና ችግር ደርሶባቸዋል (ሐዋ 8:1)። ስለዚህ አብያተ ክርስቲያናት መደጋገፍ እንዳለባቸው ያሳስባቸዋል። አብያተ ክርስቲያናት ይረዳዱ እንደነበሩም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይነግረናል "ከእነርሱም አጋቦስ የሚሉት አንድ ሰው ተነሥቶ በዓለም ሁሉ ታላቅ ራብ ሊሆን እንዳለው በመንፈስ አመለከተ፤ ይህም በቀላውዴዎስ ቄሣር ዘመን ሆነ። ደቀ መዛሙርትም እያንዳንዳቸው እንደ ችሎታቸው መጠን አዋጥተው በይሁዳ ለሚኖሩት ወንድሞች እርዳታን ይልኩ ዘንድ ወሰኑ፤" (ሐዋ 11:28-29)። ይህንንም የሚያዘው እንደየሰው የገቢ መጠን እንዲሆንና እሁድ እንዲሰበስብ ነው (16:2)።

**2. የሐዋርያው የአገልግሎት እቅድና ተቀባብሎና ተያይዞ የጌታን መንግስት ማስፋፋት (16:5-18)፡-**

ሐዋርያው ኑሮው እና ህይወቱን በሙሉ ለእግዚአብሔርና የእርሱን ሥራ ለመሥራት አስረክቧል። በመለኮታዊ ሥራው እርሱ አብሮት የሚሰራ ቢሆንም የሌሎችን አብሮ መሥራት እጅግ ጠቃሚ መሆኑን አይክድም። ለዚህ ደግሞ ቁ.6 ላይ ለጉዞው እንዲረዱት በግልጽ ይጠይቃል (2 ቆሮ 6:1)። ኢየሱስ ክርስቶስንም ሴቶች በገነዘባቸው ያገለግሉት ነበር "አሥራ ሁለቱም ከእርሱ ጋር ነበሩ፥ ከክፉዎች መናፍስትና ከደዌም ተፈውሰው የነበሩ አንዳንድ ሴቶች፤ እነርሱም ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የምትባል ማርያም፥ የሄሮድስ አዛዥ የኩዛ ሚስት ዮሐናም ሶስናም ብዙዎች ሌሎችም ሆነው በገንዘባቸው ያገለግሉት ነበር" ( ሉቃስ 8:2-3)። ወንጌል አብሮ የሚሰራ አገልግሎት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይነግረናል። ከዚህም ጋር አያይዞ ታላቅ የወንጌል በር እንደተከፈተ እና ተቃዋሚዎችም እንዳሉበት ይገልጻል (16:9)።

16፡13 ላይ ብዙ ዓይነት የተሳሳቱ ትምህርቶችና የሥነ ምግባር ጉድለቶች ቢኖሩም ጠንክረው እንዲቆሙ ይጠይቃቸዋል። ቁ. 14. በስህተት ትምህርት ባይበከሉም ከሁሉ በፊት በፍቅር መኖር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ መልዕክት ያስተላልፋል። የአንደኛ ቆሮንቶስ መልዕክት ከምዕራፍ አንድ ጀምሮ እስከ ምዕራፍ አሥራ ስድስት የሚመራው ቁልፍ ቃል "ፍቅር" ነው። ለምሳሌ እንዲሆን ለዚህ መስዋዕትነት ለተሞላ አገልግሎት አብረውት ከሚሰሩት ከጠቀሳቸው ቤተ ሰብ አንዱ የእስጢፋኖስ ቤተ ሰብ ነው (16:10)።

**3. ሰላምታና ስንብት (1 ቆሮ 16:19-24)፡-** ይህ ክፍል የሚናገረው የሌሎችን አብያተ ክርስቲያናት የልባቸውን ትስስር በሰላምታ ያቀርባል። በተለይም የቤት ለቤት ቤተ ክርስቲያን ብሎ በጊዜው የነበረውን መሰብሰቢያ ቦታ ይናገራል።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. 1ቆሮ 16:1-4 ዋና መልክት ምንድ ነው? ምን ያስተምረናል?
2. ሐዋርያው ጳውሎስ ለወንጌል አገልግሎት "ሌሎች የሚሰጡ ብሎ ምሳሌ የሚጠቀመው የየት ሀገሮችን አማኞችን ነው? የስጦታው ዓላማ ምንድ ነው?
3. ከ1ቆሮ 16:6 ከሉቃስ 8:2-3 ምን እንማራለን?

4. ፲ቆሮ.16:5-7 ዋና መልዕክት ምንድ ነው?
5. በሐዋርያው አገልግሎት አብረውት ከሚሰሩት ቤተ ሰብ አንዱ የእስጢፋኖስ ቤተ ሰብ ነው (16:10-18)። ክፍሉን አንብባችሁ ተወያዩ። ከእነዚህ አማኞች ህይወት እና አገልግሎት ምን እንማራለን?
6. ፲ቆሮ 16:18 ላይ "እንደነዚህ ያሉት መታወቅ አለባቸው" የሚለው እነ ማንን ነው? ለምን?
7. ከዛሬው ጥናት በልባችን የቀረውን መልዕክት እናካፍል?
8. ዛሬም እንደዚህ የተሰጡ ወገኖችን ጌታ እንዲያስነሳ እንጸልያለን።
9. በመጨረሻም ከዚህ ጥናት የተጠቀማችሁት ነገር ካለ በመሪዎቻችሁ በኩል አሳውቃችሁ በቤ/ክናችን ባሉት ፕሮግራሞች መመስከር ትችላላችሁ።

**መደምደሚያ**

ይህ ምዕራፍ የጌታ መንግስት አብሮ በፍቅር እና በመረዳዳት የሚሰራ እንደሆነ ያስተምራል። እግዚአብሔር አብሮን የሚሰራ ቢሆንም እኛም አብረን ወይም የአንዱ ሀገር አብያተ ክርስቲያናት ከሌሎች አብያተክርስቲያናት ጋር አብረው እንዲሰሩ ጌታ የፍቅር ኃላፊነት ሰጥቶናል።

ቤታችሁ፣ኑራአችሁ እና አገልግሎታችሁ ሁሉ የተባረከ ይሁን!!!